## ምዕራፍ 13

# በባህላዊ እምነቶችና ልምምዶች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት

«ከስድስት ቀንም በኋላ ኢየሱስ ጴጥሮስንና ያዕቆብን ወንድሙንም ዮሐንስን ይዞ ወደ ረጅም ተራራ ብቻቸውን አወጣቸው። በፊታቸውም ተለወጠ፣ ፊቱም እንደ ፀሐይ በራ፣ ልብሱም እንደ ብርሃን ነጭ ሆነ። እነሆም፣ ሙሴና ኤልያስ ከእርሱ ጋር ሲነጋገሩ ታዩአቸው። ጴጥሮስም መልሶ ኢየሱስን፦ ጌታ ሆይ፥ በዚህ መሆን ለእኛ መልካም ነው፤ ብትወድስ፥ በዚህ ሦስት ዳስ አንዱን ለአንተ አንዱንም ለሙሴ አንዱንም ለኤልያስ እንሥራ አለ» (ማቴ. 17፡1-4)።

ያኩቡ ዘመዶቹን ጎብኝቶ እየተመለሰ ነበር። የእርሻውን ሥራ በማከናወኑ ረገድ እገዛ ሲያደርግ፥ ለሦስት ሳምንታት ያህል በአጎቱ መንደር ሰንብቶ ነበር። ወደ መንደሩ ሊደርስ በተጠጋ ጊዜ፥ አንዲት አነስተኛ የምንጭ ውኃ ዘንድ ቀረበ። ምንጭዋንም ሲያቋርጥ ለረዥም ዓመታት የሚያውቃቸውን ባባ ይኑሳ የተባሉ ሽማግሌ አገኘ። ለሽማግሌው ሰላምታ ከሰጠ በኋላ፥ ስለ ቤተሰቡ ደኅንነት ጠየቃቸው።

የሚገርመው ባባ ይኑሳ ለሰላምታው አጸፋ ሊመልሱለት አልቻሉም። ያኩቡ ደጋግሞ ቢያናግራቸውም መልስ አልሰጥ አሉት። ምን እንደ ነካቸው ቢጠይቅ እንኳ፥ ሽማግሌው ባባ ይኑሳ ዝም አሉ። ያኩቡ በጣም ተጨነቀ። ይሁንና ወደ መንደሩ የሚያደርገውን ጉዞ ቀጠለ። ወደ ቤቱም በደረሰ ጊዜ፥ ያጋጠመውን ለቤተሰቡ ካጫወተ በኋላ፥ በይኑሳ ቤተሰብ ላይ የደረሰ የሚያውቁት ችግር እንዳለ ጠየቃቸው። የያኩቡ ቤተሰቦች በመገረም ትክ ብለው ተመለከቱትና፥ «አሁ፥ አይፈረድብህም። ለሦስት ሳምንታት እዚህ ስላልነበርህ ያወቅኸው ነገር የለም። ከሦስት ቀናት በፊት ባባ ይኑሳን ቀብረናቸዋል!» አሉት።

ይህ የያኩቡ ታሪክ ባህላዊ እምነቶችንና ልምምዶችን በተመለከተ አያሌ ጥያቄዎችን ያስነሣል። እውነተኛውና እውነት ያልሆነው የትኛው ነው? በአፍሪካ ባሕላዊ ሃይማኖቶች ውስጥ ትክክል የሆኑና ትክክል ያልሆኑ እምነቶች የትኞቹ ናቸው?

በአፍሪካ ባህላዊ ሃይማኖት፥ በሕያዋንና በቅርቡ በሞቱት (ሕያዋን ሙታን) መካከል በጣም አስፈላጊ የሆነ ግንኙነት አለ። የባህላዊ ሕይወት አያሌ ገጽታዎች በሕያዋንና በሕያዋን ሙታን መካከል የሚገኘውን ልዩነት ይመለከታሉ። በብዙ የሕዝብ ቡድኖች እምነት፥ የጎሳው ማኅበራዊና ግብረ-ገባዊ ጽኑነት ከዚህ በፊት ሞተው ወደ ቅድመ-ትውልዳዊ መንፈስነት ማዕረግ የተለወጡ የጎሳ መሪዎች ኃላፊነት ተደርጎ ይወሰዳል። ከጎሳው ባህላዊና ማኅበራዊ ሥርዓት ጋር በሚዛመዱ ጉዳዮች የቅድመ-ትውልዶችን ፈቃድ ችላ ማለት ትልቅ ጥፋት ነው።

ኢየሱስ መልኩ በተለወጠበት ተራራ ላይ ከሙሴና ከኤልያስ ጋር መነጋገሩ፥ የሞቱት ሰዎች ከሥጋዊ ሞት በኋላ ንቁዎች ሆነው እንደሚኖሩ የሚያስተምረውን የባህላዊ ሃይማኖቶች እምነት በግልጽ ያጠናክራል። ሙሴ ከክርስቶስ ልደት 1200 ዓመታት ቀደም ብሎ ሲሞት፥ ኤልያስም ከክርስቶስ ልደት ከ700 ዓመታት በፊት በሕይወት ሳለ ተወስዷል። ይሁንና፥ በዚህ ጊዜ ሐዋርያው ያዕቆብ፥ ጴጥሮስና ዮሐንስ ሙሴና ኤልያስ ከኢየሱስ ጋር ሲነጋገሩ ተመለከቱ። በመሆኑም፥ ሥጋዊ ሞት ወደ መንፈሳዊ ዓለም መሸጋገሪያ ድልድይ እንደ ሆነ የሚያመለክተው የአፍሪካውያን አመለካከት ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር እውነት ነው። ይሁንና፥ ከመንፈሳዊ ዓለም እውነታ የሚመነጩ አንዳንድ የባህላዊ ሃይማኖት እምነቶችና ልምምዶች ፍጹም ስሕተት በመሆናቸው፥ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ግንኙነት እንዳያደርጉ እንቅፋት ይሆናሉ።

ሰይጣን ሰዎችን የሚያታልልባቸው ብዙ መንገዶች አሉት። በዓለም ሁሉ ክርስቲያናዊ ባልሆኑ ሃይማኖቶች፥ መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስተምረን የእውነት ብርሃን እየተረዳን ልንገነዘባቸው የሚገቡ አንዳንድ ልምምዶች አሉ። እነዚህም ልምምዶች ከሙታን ጋር መነጋገርን፥ ነጭና ጥቁር ምትሐትን (መድኃኒት፥ ድግምት፥ ጥንቆላ)፥ በአጋንንት መያዝን፥ ጥራ ገላጭነትን (ያሁኑን ወይም የወደፊቱን ከስተቶች የመተንበይ መንገዶች)፥ የሽግግር ሥርዓቶችንና ሌሎችንም ይጨምራሉ። ሰዎች በተገለጸው ኃይል ወደ እነዚህ ልምምዶች ይሳባሉ። ሰዎች ዓለማቸውን ይቆጣጠሩ ዘንድ ኃይልን ይሻሉ።

ምንም እንኳ በዛሬዪቱ አፍሪካ የሕይወት ለውጥ እየታየ ቢሆንም፥ የባህላዊ እምነቶችና ልምምዶች ጥያቄ አሁንም በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ባህላዊ እምነቶች ሰዎች የእግዚአብሔርን እውነት እንዲገነዘቡ

***መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙታን ሁኔታና ከእነርሱ ጋር ስለሚኖረን ግንኙነት ምን ይላል?***

በኢየሱስ፥ በሙሴና በኤልያስ መካከል የተደረገው ውይይት እንደሚገልጽልን፥ የሞቱ ሰዎች ንቁዎች ሆነው መኖር እንደሚቀጥሉ መናገሩ ትክክል ነው። በሕይወት ዘመናቸው የተፈጸመውን የሚያስታውሱ ሲሆን፥ ሙሴና ኤልያስ በቅርቡ በኢየሩሳሌም ከተማ ስለሚፈጸመው ሞቱ ከክርስቶስ ጋር የመነጋገራቸው እውነታ እንደሚገልጸው፥ ተጨማሪም እውቀት ያላቸው ይመስላል (ሉቃ. 9:31)። ኢየሱስ ስለ ሀብታሙ ሰውዬና አልዓዛር በሉቃስ 16:19-31 የተናገረው ታሪክ ከሞት በኋላ ስለሚሆነው ነገር ተመሳሳይ ግንዛቤ የሚያስጨብጠን ሲሆን፥ ስለ ሙታን ሁኔታ የሚያስረዳን ሌላም አስፈላጊ የሆነ መረጃ አለ። ለምሳሌ፥ ሀብታሙ ሰውዬ ሲሞት እግዚአብሔርን ባለማገልገሉ የፈጸመውን ትልቅ ስሕተት በጸጸት ያስታውስ ነበር። ስለ ስሕተቱ ለወንድሞቹ ይናገር ዘንድ አልዓዛር እንዲላክ በጣም ፈልጎአል (ሉቃ. 16:25-28)። ይሁንና፥ ጥያቄው አዎንታዊ ምላሽ አላገኘለትም (ሉቃ. 16:29-31)። በተራራው ላይ ሙሴና ኤልያስ ከኢየሱስ ጋር ባደረጉት ውይይት ውስጥ፥ ምንም እንኳ ጥንታዊዎቹን ነቢያት ቢመለከቱና ንግግራቸውንም ቢሰሙም፥ ሐዋርያቱ የተናገሩት ነገር አልነበረም።

እነዚህ ታሪኮች በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ የቀረበውን እውነት ይገልጻሉ። እግዚአብሔር ሕያዋን ከሙታን ጋር እንዲነጋገሩ አይፈልግም። በዘዳግም 18:10-11 ጌታ፥ «ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው» ሲል ያስጠነቅቃል። ይህ ማስጠንቀቂያ ለምን እንደ ተሰጠ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እንነጋገራለን።

በተጨማሪም፥ በሉቃስ 16:19-31 የቀረበው ታሪክ በሞት ጊዜ በሕይወት ሳሉ እግዚአብሔርን ይወዱና ያገለግሉ የነበሩት ሰዎች መናፍስት ይህንኑ ካላደረጉት ጋር ለዘለቄታው እንደሚለያዩ ይገልጻል። አልዓዛር እግዚአብሔርን ይወድ የነበረ ድሀ ነበር። ሲሞት መላእክት ወደ መጽናኛ ስፍራ አጅበው ወሰዱት (ቁጥር 22፥ 25)። ሀብታሙ ራሱን ብቻ ይወድ ነበርና፥ ወደ ሥቃይ ስፍራ ተወሰደ (ቁጥር 23፥ 24)። በዚህ ስፍራ ኢየሱስ በሞት ጊዜ ሰዎች ከሰዎች እንደሚለዩና ኃጢአታቸው ያልተሰረየላቸው ሰዎች ለሥቃይ እንደሚወሰዱ የሚያስረዳ አሳዛኝ እውነት ገልጾአል።

በብሉይ ኪዳን ውስጥ በሚገኝ አንድ ታሪክ፥ ንጉሥ ሳኦል ነቢዩ ሳሙኤል ከሞተ በኋላ ከመንፈሱ ጋር ለመነጋገር እንደ ፈለገ ተገልጾአል (1 ሳሙ. 28:8-19)። እርሱ ራሱ በእግዚአብሔር ሕግ መሠረት ከዚህ በፊት ይኸው ልምምድ በእስራኤል እንዳይፈጸም የከለከለ በመሆኑ፥ ንጉሥ ሳኦል ሙትን በማማከሩ ትክክል ያልሆነ ተግባር መፈጸሙን ያውቅ ነበር (ዘሌ. 19:31፤ 1 ሳሙ. 28:9)። ሳኦል ከሙታን ጋር ለመነጋገር የፈለገው ከችግሩ የተነሣ ነበር (1 ሳሙ. 28:15)።

የሳሙኤል መንፈስ ለሳኦል በታየ ጊዜ፥ ሳሙኤል እግዚአብሔርን መታዘዝ እንደ ነበረበት በመግለጽ ጠንካራ የኩነኔ ቃል ሰነዘረበት (1 ሳሙ. 28:16-19)። እግዚአብሔር ሳሙኤል ሳኦልን በዚህ ባልተለመደ ሁኔታ እንዲያበረታታው ወይም እንዲረዳው ሳይሆን፥ እንዲኮንነው ፈቀደ። ከዚህ ታሪክ እግዚአብሔር ሕያዋን ከሙታን ጋር እንዲነጋገሩ እንደማይፈልግ ልንመለከት እንችላለን። በብዙ ባህላዊ ሃይማኖቶች እንደሚታሰበው፥ ከሙታን ጋር መነጋገር ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣ የእርዳታ ወይም የማበረታቻ ምንጭ እንዳልሆነ እንመለከታለን።

የሚሞቱ ክርስቲያኖች ምን ይሆናሉ? ኢየሱስ በመሞት ሂደት ላይ ለነበረው ወንጀለኛ እንደ ተናገረው (ሉቃ. 23:41-43) እና ጳውሎስም እንደሚለው (2 ቆሮ. 5:1-8)፥ ክርስቲያኖች ሲሞቱ ክርስቶስ ወዳለበት ገነት (መንግሥተ ሰማይ) ይሄዳሉ። ሙታን ሁሉ ከመነሣታቸው በፊት በሚሆነው በዚህ የሽግግር ወቅት፥ አማኞች እርስ በርሳቸው የሚነጋገሩበትና የሚግባቡበት ሰማያዊ አካል ይሰጣቸዋል (2 ቆሮ. 5:1-4)። ኢየሱስ በተራራ ላይ በተናገራቸው ጊዜ ጴጥሮስ፥ ያዕቆብና ዮሐንስ የሙሴንና የኤልያስን ሰማያዊ አካላት አይተው ንግግራቸውንም ሰምተዋል (ሉቃ. 9:28-32)።

የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ክርስቲያኖች በሚሞቱበት ጊዜ በቀጥታ ከጌታ ጋር ለመኖር የሚሄዱት እጅግ በጣም ጥቂቶች (እነርሱም ካሉ) እንደ ሆኑ በመግለጽ የምታቀርበውን ትምህርት ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት አይቀበሉትም። ካቶሊኮች ክርሲቲያኖች በመጀመሪያ በእሳት ወደሚነጹበት የማጣሪያ ስፍራ ይወሰዱና ከዚያ በኋላ ወደ መንግሥተ ሰማይ እንደሚገቡ ያስተምራሉ። ይህም ማጣሪያ ስፍራ «ፐርጋቶሪ» ("purgatory") በመባል ይታወቃል። ይህ አሳብ ከብዙ የአዲስ ኪዳን ትምህርቶች ጋር ይቃረናል። ጳውሎስ «ከሥጋ ተለይተን . . . በጌታም

ዘንድ ማደር ደስ ይለናል» ይላል (2 ቆሮ. 5፡8)። ጳውሎስ በተጨማሪም፥ ክርስቶስ ስለ እኛ ስለ ሞተ፥ በሥጋ ሙታን ወይም ሕያዋን ብንሆን ከክርስቶስ ጋር አብረን እንደምንኖር አስተምሮአል (1 ተሰ. 5፡10)። ኢየሱስ ከእርሱ አጠገብ በመስቀል ላይ ለተሰቀለው ሌባ፥ «ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ» ብሎታል (ሉቃ. 23፡43)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እነዚህና ሌሎችም ጥቅሶች እንደሚያመለክቱት፥ ይቅርታ ያገኘ ኃጢአተኛ በሚሞትበት ጊዜ፥ በቀጥታ ክርስቶስ ወደሚገኝበት ወደ ገነት ይገባል።

ከክርስቶስ ጋር የሚያድን የግል ግንኙነት ሳያደርጉ የሚሞቱትስ ሰዎች? ኢየሱስ ራሱ ለአይሁዶች፥ «በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁ አልኋችሁ እኔ እንደሆንሁ ባታምኑ በኃጢአታችሁ ትሞታላችሁና» ሲል ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ሰጥቷል (ዮሐ. 8፡24)።

የኃጢአትን ይቅርታ ሳያገኙ መሞት የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው? በሀብታሙ ሰውዬና በአልዓዛር ታሪክ ውስጥ ኢየሱስ ከሞት በኋላ ምን እንደሚሆን ገልጾአል። የሁለት ሙታንን ሁኔታ ገልጾአል። ኢየሱስ ራስ ወዳድ ሆኖ እግዚአብሔርን ለማገልገል የሌሎችን ሰዎች ጉድለቶች ለመሙላት ግድ ያልነበረው ሀብታሙ ሰው ወደ ሥቃይ ስፍራ እንደ ተወሰደ ገልጾአል (ሉቃ. 16፡23-24)። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በሰው ዘር ላይ ስለሚመጣው የመጨረሻው ፍርድ ሲናገር፥ የእርሱ ያልሆኑት ሁሉ ወደ ሥቃይ ስፍራ እንደሚሄዱ ገልጾአል (ማቴ. 25፡31-46)።

### ለ. ክርስቲያን ከቅድመ-ትውልዶች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት፥ መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል?

ብዙውን ጊዜ ባህላዊ ሃይማኖቶች በሕያዋንና በሕያዋን ሙታን መካከል ግንኙነቶችን ለማድረግ ይፈልጋሉ። እነዚህም ግንኙነቶች ሥርዓቶችንና ቅድመ-ትውልዶችን (አያት ቅድማያት) ለማርካት ወይም ለማግባባት የሚያደርጉትን መሥዋዕቶች ያጠቃልላሉ። በተጨማሪም፥ በሞራ ገላጭ ወይም መንፈሱ በያዛቸው ሰዎች አማካኝነት በቀጥታ በሚነገሩ ቃላት ከሙታን ጋር መነጋገርን ይጨምራሉ። እነዚህ ባህላዊ እምነቶች ሁልጊዜም ለማለት ይቻላል ሕያዋን ለምሪት፥ ለእርዳታ፥ ለእርምትና ለበረከት በቀጥታ ወደ እግዚአብሔር ከሚመለከቱ ይልቅ፥ ወደ አያት ቅድማያቶቻቸው ወይም ወደ ሌሎች መናፍስት እንዲመለከቱ ያደርጋሉ። ይህንንም በማድረግ፥ እንዲህ ዓይነት ሰዎች እግዚአብሔር ከእርሱ በፊት

ሌላ ማናቸውም ዓይነት «አማልክት» እንዳይኖሩ የሰጠውን የመጀመሪያውን ትእዛዝ ይጥሳሉ (ዘጸ. 20፡3)።

የአያት ቅድማያት መናፍስት የሚካተቱባቸው ባህላዊ እምነቶችና ልምምዶች ከእግዚአብሔር አይደሉም። እነዚህ ሰይጣን ሰዎችን ለማሳሳትና ትእዛዛቱን በመጣሳቸው ከእግዚአብሔር ፍርድ በታች እንዲወድቁ ለማድረግ የሚጠቀምባቸው ስውር ዕቅዶች አካል ናቸው። ከአያት ቅድማያት መናፍስት ጋር የሚዛመዱ እምነቶችና ልምምዶች፥ ብዙ ሰዎች በኢየሱስ ክርስቶስ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት እንዳያደርጉ አግደዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሰው ከወላጆቹና በማኅበረሰቡ ውስጥ በዕድሜ ከገፉት ሰዎች ጋር ስለሚኖረው ግንኙነት ምን ይላል? መጽሐፍ ቅዱስ አጠቃላይ መመሪያ ይሰጠናል፡- «በሽበታሙ ፊት ተነሣ፥ ሽማግሌውንም አክብር፥ አምላክህንም ፍራ፤ እኔ እግዚአብሔር ነኝ» (ዘሌ. 19፡32)። ይህ ከሙሴ ሕግ የተወሰደው ዓረፍተ ነገር ሰዎች ለሽማግሌዎች ሁልጊዜም አክብሮት መስጠታቸው ትክክልና በእግዚአብሔርም ፊት ደስ የሚያሰኝ እንደ ሆነ ይገልጻል። እንዲያውም፥ የዚህ ዓይነቱን አክብሮት ማሳየት ራሱ እግዚአብሔርን ከመፍራት ጋር በሆነ መንገድ መገናኘቱም ተጠቁሟል።

ሰው ከራሱ ወላጆች ጋር ስለሚኖረውስ ግንኙነት? ከአሥርቱ ትእዛዛት አምስተኛው፥ «እናትህንና አባትህን አክብር» ይላል (ዘጸ. 20፡12)። ይህ ትእዛዝ ሰዎች ሁሉ ወላጆቻቸውን ማክበራቸው የእግዚአብሔር ፈቃድ እንደ ሆነ ያሳያል። ወላጆቻቸውን በማክበርና ምክራቸውን በጥንቃቄ በመከተል ይህንን ሊፈጽሙ ይችላሉ (ምሳሌ 1፡8)። በሕይወት ለሚገኙ ወላጆቻቸው በመገዛትና የእግዚአብሔርን ቃል እንዲተላለፉ በማያደርጋቸው መንገድ ሁሉ ታዛዥነትን በማሳየት ይህንኑ ሊፈጽሙ ይችላሉ (ኤፌ. 6፡1፤ ቆላ. 3፡20)። ለወላጆቻቸው ሊሰጡ የሚችሉት እጅግ ከፍተኛ የአክብሮት ዓይነት መንፈሳዊ ባሕርይና ጠባይ ያለው ቅዱስ ሕይወት በመኖር ነው።

ሕያዋን ከሙታን ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት መጽሐፍ ቅዱስ ምን ይላል? በሕይወት ለሚገኙ ወላጆቻችን ከተሰጡት መመሪያዎች አንዳንዶቹ የሞቱትን ከማክበርም ጋር ይዛመዳሉ። መንፈሳዊ ባሕርይና ጠባይ ያለው የተቀደሰ ሕይወት በመኖር፥ ለስማቸው አክብሮት በመስጠት፥ በምድር ላይ በሕይወት በነበሩበት ጊዜ የሠሩአቸውን

መልካም ሥራዎች በማክበርና ክርስቲያኖች ከነበሩ የእምነት ፈለጋቸውን በመከተል፥ ለሞቱት የቤተሰባችን አባላት አክብሮት ልንሰጥ እንችላለን።

ይሁንና፥ ክርስቲያኖች አያት ቅድማያቶቻቸውን ሲያከብሩ ወደ ባህላዊ ሃይማኖት እምነቶችና ልምምዶች እንዳይመለሱ ጥንቃቄ ማድረግ አለባቸው። ክርስቲያናዊ ባልሆኑ ሃይማኖቶች በተለምዶ እንደሚደረገው፥ እግዚአብሔርን በማክበር ፈንታ አያት ቅድማያቶቻቸውን እንዳያከብሩ መጠንቀቅ አለባቸው። ክርስቲያን ለሕይወቱ ምሪት፥ እርምት፥ እገዛና በረከት ለማግኘት፥ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደ እግዚአብሔር ብቻ ሊቀርብ ይገባዋል። አንድ ሰው ችግር ሲገጥመው፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ወደ እግዚአብሔር አብ መጸለይ አለበት። አንድ ሰው ከራሱ ከእግዚአብሔር ሌላ የማንኛውንም አያት ቅድማያት፥ ሞራ ገላጭ፥ ወይም መንፈስ በረከት፥ ምሪት፥ ወይም እገዛ መፈለግ የለበትም። መዝሙረኛው በጥበብ፥ «ወደ ሌላ ለሚፋጠኑት መከራቸው ይበዛል፤ የቁርባናቸውን ደም እኔ አላፈስሰውም፥ ስማቸውንም በከንፈሬ አልጠራም» ሲል ይመከረናል [መዝ. (16) :4]።

የቤተሰባቸውን አባላት እንዲያከብሩ ቢጠየቁም፥ ሕያዋን ሙታንን ለማነጋገር ወይም የሙታን ዘመዶቻቸውን እገዛ ለማግኘት ከቶውንም መሞከር የለባቸውም (ዘዳ. 18፡10-11)። እግዚአብሔር እነዚህ ሰዎች ለአያት ቅድማያቶቻቸው የምግብ ወይም የመጠጥ መሥዋዕት እንዲያቀርቡ አይፈልግም (ዘዳ. 26፡14)። እንዲህ ዓይነት የምግብ ወይም የመጠጥ መሥዋዕት ማቅረብ ክርስቲያናዊ ሃይማኖቶች ያልሆኑትን የአረማውያን ልምምድ መከተል ነው። ይህም እግዚአብሔር የሚከለክለው የጣዖት አምልኮ ዓይነት ነው (ዘጸ. 20፡18)። በምዕራፍ 11 እንደ ተመለከተው፥ የዚህ ዓይነት መሥዋዕቶች ለአያት ቅድማያት መናፍስት ሲሠዉ፥ መሥዋዕቶቹን የሚቀበሉት ከቶውንም አያት ቅድማያቶች ሳይሆኑ አጋንንት ናቸው (ዘዳ. 32፡16፥ 17፤ 1 ቆር. 10፡19-20)።

እግዚአብሔር ሕዝቡ አያት ቅድማያቶችን ወይም ሌሎች ማናቸውንም መናፍስት በእግዚአብሔር ፊት ከሚያስቀምጡ ባህላዊ ሃይማኖቶች ጋር የሚያያዙትን ዕቃዎች እንዲያቃጥሉና እንዲያጠፉ አዝዞአል። በተጨማሪም፥ የዚህ ዓይነቶቹን እምነቶችና ልምምዶች ሙሉ ለሙሉ መተው አለባቸው። እግዚአብሔር ሕዝቡ የሆኑትን እስራኤላውያን፥ «ነገር ግን እንዲህ አድርጉባቸው፤ መሠዊያቸውን አፍርሱ፥ ሐውልቶቻቸውንም ሰባብሩ፥ የማምለኪያ ዐፀዶቻቸውንም ቁረጡ፥ የተቀረጸውን ምስላቸውንም

በእሳት አቃጥሉ» ሲል አስጠንቅቆአቸዋል (ዘዳ. 7፡5)። እግዚአብሔር ይህን ትእዛዝ በዚያው ምዕራፍ ደግሟል (ዘዳ. 7፡25)። በቤቶቻቸው ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶችን ዕቃዎች እንዳያስቀምጡ ተከልክለዋል (ዘዳ. 7፡26)። በአዲስ ኪዳን፥ የኤፌሶን ሰዎች ይህ ከኃጢአታቸው ንስሐ በገቡበት ሁኔታ ውስጥ እንደሚጠቃለል ተረድተው ነበር። ከዚህም የተነሣ፥ የኤፌሶን ሰዎች ዳግም ሲወለዱ ክርስቲያናዊ ካልሆኑ እምነቶቻቸውና ልምምዶቻቸው ጋር የተዛመዱትን ዕቃዎች አቃጥለዋል (የሐዋ. 19፡18-19)። የአፍሪካ ክርስቲያኖችም ይህንኑ ለማድረግ መማር አለባቸው።

ከባህላዊ ሃይማኖት በግልጽ ለዘለቄታው አለመለየት የአፍሪካን ቤተ ክርስቲያን በእጅጉ ጎድቶአታል። ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ልምምዶችንሙሉ ለሙሉ አለማስወገድ የከፋ ኃጢአት በመሆኑ፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ ያስከትላል፤ ከአንድ ሰው ሕይወት የእግዚአብሔርን ጥበቃ ሊያሳጣ ይችላል። እስራኤላውያን በዙሪያቸው የሚገኙትን ሕዝቦች ባህላዊ ሃይማኖቶች ሙሉ ለሙሉ ባለማስወገዳቸው፥ እግዚአብሔር፥ «እናንተ ግን ተዋችሁኝ ሌሎችንም አማልክት አመለካችሁ፤ ስለዚህም ደግሞ አላድናችሁም። ሄዳችሁም የመረጣችኋቸውን አማልክት ጥሩ፤ እነርሱም በመከራችሁ ጊዜ ያድኑአችሁ» ብሏል (መሳ. 10፡13-14)። ይህም ብዙ የአፍሪካ ክርስቲያኖች ከኀሰኛነትና ቅይጥ አምልኮ በሚመነጩ ችግሮች ለምን እንደሚሠቃዩ በከፊል ሊያብራራ ይችላል።

### ሐ. የሙታንን መናፍስት በተመለከተ፥ እውነቱ ምንድን ነው? በአጋንንት የመታለል ውጤቱ ምንድን ነው?

መናፍስት ባብዛኛዎቹ የዓለም ክፍሎች በአንድ ወይም በሌላ ጊዜ ታይተዋል። እነዚህም መናፍስት ብዙውን ጊዜ አያት ቅድማያት እንደ ሆኑ ይናገራሉ። ቁርጥ የሞቱትን ዘመዶች ሊመስሉና እንደ እነርሱም ሊናገሩ ይችላሉ። በአንዳንድ ስፍራዎች መናፍስት ("ghosts") ተብለው ይጠራሉ።

እነዚህ መናፍስት እነማን ናቸው? በምዕራፍ ስድስት እግዚአብሔር ለሞቱት ሰዎች መናፍስት የተወሰነ ስፍራ እንደሚመድብና ከዚያም ስፍራ እንደማያስወጣቸው ተመልክተናል (ሉቃ. 16፡24-26፤ 2 ቆር. 5፡8)። ልክ እንደ ነቢዩ ሳሙኤል (1 ሳሙ. 28፡15-19) ልዩ ፈቃድ እስካልተሰጣቸው ድረስ፥ ከዚያ ስፍራ ሊንቀሳቀሱ አይችሉም። በመሆኑም፥ የመንፈስ መታየት የአያት ቅድማያት መታየት የመሆን ዕድል ብዙም አያወላዳም።

አጋንንት በፈለጉት መንገድ ለሰዎች ሊታዩ ስለሚችሉና (2 ቆር. 11:14፤ ራእይ 16:13) ከሰዎች የላቀ ኃይልና እውቀት ስላላቸው፥ የሞቱትን ዘመዶች አኳኋንና ድምፅ ተላብሰው መምጣታቸው ሊያስገርመን አይገባም። ልክ በዚህ ምዕራፍ መግቢያ ላይ እንደ ቀረበው እውነተኛ ታሪክ ሁሉ፥ የሞተውን ሰው መንፈስ እንዳዩ የሚናገሩ ሰዎች ብዙ ምስክርነቶችን ሰጥተዋል።

አጋንንት የሞቱትን ሰዎች መስለው የሚታዩት ለምንድን ነው? ይህንን የሚያደርጉት፥ ሰዎች ክርስቶስን ከማመን ይልቅ አያት ቅድማያቶችን ወይም መናፍስትን እንዲያምኑ የሚያስተምሩትን ክርስቲያናዊ ያልሆኑ አሳሳች ሃይማኖቶች ለማሳደግ ነው። የተወሰነ የመንፈስ መታየት የሞተው ሰው መንፈስ ይሁን ወይም የአጋንንት ማስመሰል በእርግጠኛነት መናገሩ አስቸጋሪ ነው። ይሁንና፥ ብዙው አጋጣሚ የአጋንንት የማሳሳቻ ክንውን እንደ ሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ መገለጽ ይነግረናል።

በቅርብ ጊዜያት፥ ዶክተሮች አንዳንድ በሽተኞችን ልባቸው መምታት ካቆመበት የሞት ጫፍ ለመመለስ ችለዋል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ ያጋጠማቸው አንዳንድ ሰዎች መንፈሳቸው ከሥጋቸው ተለይቶ እንደ ነበር ተናግረዋል። መንፈሳቸው ከሥጋቸው ሲለይ ምን እንዳደረጉና ማንን እንዳዩ በትክክል እንደሚያስታውሱ ይናገራሉ። አንዳንዶች መንግሥተ ሰማይን ወይም ሲኦልን እንዳዩ ይተርካሉ።

የማያምኑ ሰዎች ከሚናገሩአቸው ከእነዚህ ታሪኮች አንዳንዶቹ፥ መጽሐፍ ቅዱስ ከሞት በኋላ ስለሚሆነው ነገር ከሚያስተምረው ጋር አይስማሙም። ለምሳሌ፥ አንዳንዶች ከሞት በኋላ ሰዎች ኃጢአታቸው የሚሠቃዩበት ሲኦል የሚባል ስፍራ እንደሌለ ይናገራሉ። የዚህ ዓይነቱ የውሸት ምስክርነት የሚሰጠው ለብዙ ምክንያቶች ሊሆን ይችላል። አንዳንድ ጊዜ የልቡ ምት ሲቆም የሰውየው (የሴትዮዋ) አንጎል ሊነካ ይችላል። በሌላ በኩል፥ ሰውዬው በአጋንንት ተታሎ ይሆናል። በተጨማሪም፥ በእንዲህ ዓይነቶቹ ከሥጋ የመለየት አጋጣሚዎችና በመጽሐፍ ቅዱስ በተገለጸው እውነተኛ ሞት መካከል ልዩነት እንዳለ ልብ ልንል ይገባል። በእውነተኛ ሞት ጊዜ፥ የሰውዬው የሰብአዊነት መንፈስ ለዘለቄታው ይለየዋል።

አንዳንድ ሰዎች ከሙታን ጋር እንደ ተነጋገሩ ይገልጻሉ። በዚህ ዓይነት አጋጣሚዎች፥ የ«ሞተው» ሰውዬ ቃላት ከእግዚአብሔር ጋር የማይስማሙ ከሆነ፥ ከሞተ ሰው ጋር እንደ ተነጋገሩ የሚያስቡ ሰዎች ተታለዋል። የራሳችን አእምሮ ሊያታልለን ይችላል። አጋንንት በቀላሉ ሰዎችን

እንዲይዙ ግብዣ ያቀርቡላቸዋል። ምንም እንኳ የሚጋብዙአቸው ሰዎች ችር የአያት ቅድማያት መናፍስትን ወይም ደጋግ አማልክትን እንደሚጋብዙ ቢያስቡም፥ አጋንንት የእነዚህን ሰዎች ሕይወት ለመቆጣጠር ፍጹም ፈቃደኞች ናቸው።

ራሳቸውን ለኃጢአት አሳልፈው በሚሰጡ ሰዎች ሕይወት ሰይጣን የሚያገኘው በር ምን ያህል የሰፋ ይሆን? የሰው ታሪክ ጭካኔ የሞላበት ገጽታ ለዚህ ጥያቄ አንደኛው ምላሽ ነው። በአጋንንት ተጽዕኖ በሰዎች ሕይወት ምን ያህል የግድያ ወንጀሎች፥ የነገድ ጦርነት፥ ሥቃይና ሴቶችን አስገድዶ የመድፈር ተግባራት እንደ ተፈጸሙ ስናስብ ከመደነቅ በቀር የምንጨምረው የለንም። አንደኛው የከፋት ገጽታ በራሳቸው ምሳሌነት፥ አሳቦች፥ ወይም አግባብነት በጎደላቸው ተግባራት፥ ለልጆቻቸው ኃጢአትን የሚያስተዋውቁትን ክርሲቲያን ያልሆኑ ወላጆች የሚመለከት ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የወላጆች ኃጢአት እስከ ሦስትና አራት ትውልድ ድረስ በልጆች ላይ እንደሚቆጠር ይገልጻል (ዘጸ. 34:7)። ይህ በተለይ ወላጆች በሕይወታቸው ከእግዚአብሔር መንፈስ ባሻገር ሌሎችን መናፍስት በሚያስተናግዱበት ስፍራ እውነት ነው (ዘጸ. 20:5)። ምናልባት ብዙ ልጆች በሕፃንነታቸው በአጋንንት የሚያዙበትና በሌሎችም ተጽዕኖዎች የሚሠቃዩበት አንዱ ምክንያት ይኸው ይሆናል።

መጽሐፍ ቅዱስ በመንፈስ መያዝ የአጋንንት ሥራ እንደ ሆነ በግልጽ ይናገራል። መጽሐፍ ቅዱስ ኢየሱስ ሰዎችን ከመናፍስት ተጽዕኖ ስላዳነበት ሁኔታ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲገልጽ፥ «በመሸም ጊዜ አጋንንት ያደረባቸውን ብዙዎችን ወደ እርሱ አመጡ . . . መናፍስትን በቃሉ አወጣ፥ የታመሙትንም ሁሉ ፈወሰ» ይላል (ማቴ. 8:16)። በዚህ ስፍራ ሰዎችን የሚይዙ መናፍስት በግልጽ አጋንንት ተብለው ተጠርተዋል። በሐዋሪርያት ሥራ መጽሐፍ ኢየሱስ ሰዎችን በመፈወስና አጋንንትን በማስወጣት ያበረከተው አገልግሎት፥ እንደሚከተለው ጠቅለል ብሎ ተገልጾአል:- «እግዚአብሔር የናዝሬቱን ኢየሱስን በመንፈስ ቅዱስ በኃይልም ቀባው፥ እርሱም መልካም እያደረገ ለዲያብሎስም የተገዙትን ሁሉ እየፈወሰ ዞረ፥ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ነበረና» (የሐዋ. 10:38)።

### ሠ. የአጋንንት ተጽዕኖ የደረሰባቸውን ወይም በአጋንንት ቁጥጥር ሥር የወደቁትን ሰዎች ክርስቲያኖች እንዴት ሊረዱአቸው ይችላሉ?

ክርስቲያኖች በኢየሱስ ስም አጋንንት እንዲያስወጡ ክርስቶስ ራሱ ሥልጣን ሰጥቶአቸዋል (ማር. 16:17፤ ሉቃ. 9:1፤ 10:17፥ 19)።

ክርስቲያኖች ከሥልጣናትና አጋንንታዊ ኃይላት ሁሉ በላይ በመንፈሳዊ ሁኔታ ከክርስቶስ ጋር ስለ «ተቀመጡ» (እንደ አካሉ ከክርስቶስ ጋር ስለ ተጣመሩ)፥ ይህ ሥልጣን በእጃቸው ነው (ኤፌ. 1፡19-22፤ 2፡6)። በመንፈስ የተያዘው ሰው የሚሠቃየው ከአጋንንታዊ ጥቃት እንጂ ከተራ የጠባይ ለውጥ እንዳልሆነ ሲረጋገጥ፥ ክርስቲያኑ አጋንንቱን ለማስወጣት የሚሞክር ከሆነ የኃይል ተግዳሮት ይኖራል።

ለአጋንንት መኖር መሠረቱ ኃጢአት እንደ መሆኑ፥ በአጋንንት የተያዘው ሰው ኃጢአቱን ለመናዘዝና ለመተው፥ ብሎም ክርስቲያናዊ ያልሆኑ እምነቶቹንና ልምምዶቹን ለማስወገድ ካልፈለገ፥ ለዘለቄታው ከአጋንንት ጥቃት ለመላቀቅ አይችልም። እንዲህ ዓይነት ኑዛዜና ኃጢአትን የመተው ተግባር ለመፈጸም ከማይፈልግ ሰው አጋንንት ለማስወጣት መሞከር ጥበብ የጎደለውና አደገኛ የሆነ ልምምድ ነው። ማንኛውም ዓይነት ስኬታማ አጋንንትን የማያስወጣት ተግባር ከመፈጸሙ በፊት፥ ግልጽ የሆኑትን ኃጢአቶች መናዘዝና ማስወገድ የግድ አስፈላጊ ነው።

አንዳንድ ሰዎች ሙሉ ለሙሉ በአጋንንት ተጽዕኖ ሥር ስለሚወድቁ፥ በሰውዬው ምትክ አጋንንቱ ይናገራል (ማር. 5፡9-10)። እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ፥ ክርስቲያኖች ከሰዎቹ ጋር ስለ ኃጢአታቸውና ንስሐ መግባትም እንደሚያስፈልጋቸው ለመነጋገር፥ አጋንንቱን ማሰር፥ ዝም ማሰኘት ወይም ማስወጣት አለባቸው። በአጋንንት የተያዙትን ሰዎች ለማማከር፥ በመጀመሪያ ደረጃ አጋንንት ጥቃት ለማድረስ ወይም ፈንታ ለማግኘት የቻሉበትን ኃጢአት ማወቅ ያሻል። ለዚህም፥ ሰዎቹ ቢያንስ ለጊዜውም ቢሆን፥ አጋንንት በአእምሮአቸውና በስሜታቸው ላይ ከሚያስከትሉት ተጽዕኖ መላቀቅ አለባቸው። ስለ ሆነም፥ አጋንንትን በኢየሱስ ስም ዝም ማሰኘት ወይም ማስወጣት አስፈላጊ ይሆናል። ይሁንና፥ አጋንንት ውሸታሞችና በማታለልም የተካኑ በመሆናቸው ከእነርሱ ጋር መነጋገሩ አላስፈላጊ ነው።

ሰውዬው ለዘለቄታው ከአጋንንታዊ ተጽዕኖ ከመላቀቁ በፊት፥ ማጋለጥ፥ መናዘዝና መተው የሚያስፈልገው መሠረታዊ ነገር ኃጢአቱን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በዋናነት ስለ ኃጢአት እየተናገረ በጥቂቱ ብቻ ስለ አጋንንት የሚናገረው ለዚህ ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፥ ንስሐ መግባት ኃጢአትንና የሰይጣን ሥራዎች ሁሉ መካድን ያጠቃልላል። በቀድሞዪቱ የክርስቲያን ቤተ ክርስቲያን እንዲህ ዓይነቶቹ ክህደቶች፥ «አንተን ሰይጣንን፥ ሥራዎችህንና መንገዶችህን ሁሉ እክዳለሁ» በሚል ዓረፍተ ነገር፥ የሰውዬው የጻግም ልደት አካል ተደርገው ይዘወተሩ ነበር።

በአንዳንድ አጋጣሚዎች ዛሬ ይህ አስቀድመው የሞቱትን ጨምሮ፥ የወላጆችን ወይም የሌሎች ዘመዶችን አላግባብ ልምምድ ወይም የኃጢአት ተጽዕኖ መካድን ሊያካትት ይችላል! አንድ ሰው ኃጢአቱን ከካደ በኋላ፥ በክርስትና እምነት በትዕግሥት ማስተማርና ማበረታታት አስፈላጊ ነው፤ ይህ ካልሆነ ወደ ቀድሞ ኃጢአቱ ይመለስና ለበለጠ አጋንንታዊ ወረራ ራሱን ያጋልጣል።

አጋንንት ከሚቆጣጠሩአቸው ሰዎች ሲወጡ ይናደዳሉ። የወጡባቸውንም ሰዎች በብዙ መንገዶች ለማጥቃትና ለመጉዳት ይሞክራሉ። አጋንንት የወጡባቸው ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል በመታዘዝ ራስን ስለ መግዛት ብዙ ሊማሩ ይገባል። እንዲሁም፥ ሌሎች ክርስቲያኖች በድጋፍ፥ በጸሎትና በደቀ መዛሙርትነት ሊረዱአቸው ይገባል።

ጳውሎስ በኤፌሶን ሲሰብክ፥ በዚያ ስፍራ የነበረውን ክርስቲያናዊ ያልሆነ ሃይማኖት ይከተሉ የነበሩ ሰዎች፥ የሃይማኖታቸውን የመገልገያ ዕቃዎች በመሰባበርና ኃጢአታቸውን በመናዘዝ፥ ልምምዳቸውን ለመተውና ለመካድ እንደሚፈልጉ አሳይተዋል (የሐዋ. 19፥18-19)። አንድ ሰው በሕይወቱ ሙሉ ለሙሉ ከሰይጣን ተጽዕኖ እንዲላቀቅ ከተፈለገ፥ አረማዊ ወይም የኃጢአት ልምምድን እንደዚህ በግልጽ መናዘዝና መተው አስፈላጊ ነው።

እግዚአብሔር ጌዴዎንን እስራኤላውያንን ከምድያማውያን ጭቆና ነፃ እንዲያወጣ ሲጠራው (መሳ. 6፥11-14)፥ በመጀመሪያ ሕዝቡ የገነቡትን አረማዊ ጣዖት ማፍረሱ ለጌዴዎን አስፈላጊ ነበር (መሳ. 6፥25-27)። ጌዴዎን የቤተሰቡን የውሸት ሃይማኖት እስኪያስወግድ ድረስ፥ እግዚአብሔር ምድያማውያንን ያሸንፍ ዘንድ ጌዴዎንን በኃይል አያስታጥቀውም ነበር። ዛሬም እንደዚሁ፥ አንድ ሰው ክርስቲያናዊ ያልሆነ ሃይማኖትን እምነቶችና ልምምዶች በሕይወቱ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች የታወቁ ኃጢአቶች ጋር ካላስወገደ፥ እግዚአብሔር ሰይጣንን እንዲያሸንፍ አያስችለውም።

ከእንዲህ ዓይነቱ ኃጢአትን የመካድ ውሳኔ በኋላ፥ ክርስቶስን በመከተልና ለቃሉ በመታዘዝ እያደጉ ብርቱ ደቀ መዝሙር መሆን አስፈላጊ ነው። የዚህ ዓይነቱ ክትትልና ደቀ መዝሙርነት ከሌለ፥ አዲስ ያመነው ሰው ችግር ሲገጥመው ወደ ቀድሞው ክርሲትያናዊ ያልሆነ ሃይማኖቱ ሊመለስ የሚችልበት አደገኛ ሁኔታ ይኖራል። በአፍሪካ ብዙ ክርስቲያኖች በችግራቸው ጊዜ ወደ ባህላዊ ልምምዶች የሚመለሱት፥

ጥንታዊ የተመሳበት የደቀ መዛሙርነት ክትትል ባለመደረጉ ነው። ዛሬ ለአፍሪካ ቤተ ክርስቲያን ትልቁ አስፈላጊ ነገር ደቀ መዝሙርነትና ለእግዚአብሔር ቃል በመታዘዝ በክርስቶስ ወደ ብስለት ማደግ ነው።

## ረ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መንግሥተ ሰማይና ሲኦል ምን ይላል?

መጽሐፍ ቅዱስ መንግሥተ ሰማይና ሲኦል በትክክል መኖራቸውን ይገልጻል። መንግሥተ ሰማይ እግዚአብሔር የሚያድርባት ብፅዕት ስፍራ ነች። ኢየሱስ መንግሥተ ሰማይን ገነት ይላታል። ከኢየሱስ ግራና ቀኝ ከተሰቀሉት ሁለት ሌቦች አንደኛው ከኃጢአቱ ንስሐ ስለ ገባና በክርስቶስ ስላመነ፥ ክርስቶስ፥ «ዛሬ በገነት ከእኔ ጋር ትሆናለህ» ብሎታል (ሉቃ. 23:43)። ሐዋርያው ጳውሎስ፥ «እንዲህ ያለው ሰው ከአሥራ አራት ዓመት በፊት እስከ ሦስተኛው ሰማይ ድረስ ተነጠቀ . . . ወደ ገነት ተነጠቀ፥ ሰውም ሊናገር የማይገባውን የማይነገረውን ቃል ሰማ» ብሏል (2 ቆሮ. 12:2-4)። በራእይ 21:2–22:15፥ ሐዋርያው ዮሐንስ መንግሥተ ሰማይን «ቅድስቲቱ ከተማ፥ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም» በማለት ይገልጻታል (ራእይ 21:2)።

ከዚህ በፊት መንግሥተ ሰማይን አይተው ወደ አካላቸው እንደ ተመለሱ ከተጠቀሱት ሰዎች አንዳንዶቹ፥ ቅድስቲቱን ከተማ ልክ በመጽሐፍ ቅዱስ እንደ ተገለጸችው አድርገው አብራርተዋል። ሐዋርያው ዮሐንስ አንዳንዶች በቀጥታ ሌሎች ደግሞ በተምሳሌትነት የሚተረጉሟትን ቅድስቲቱን ከተማ በዝርዝር ገልጾአታል (ራእይ 21:10-27)። የፍጻሜው እውነታ ቅድስቲቱ ክተማ ማንኛውም ሰው ለመቼውም ከሚገልጸው በላይ የላቀችና የከበረች መሆኗ ነው። በምዕራፍ አሥራ ስምንት መጨረሻ አካባቢ ስለ መንግሥተ ሰማይና ስለ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር መንግሥት ተጨማሪ ማብራሪያ ይቀርባል።

እንደ ተመለከትነው፥ መጽሐፍ ቅዱስ የሞተ ሰው መንፈስ እግዚአብሔር ወዳለበት ስፍራ (መንግሥተ ሰማይ) ወይም ወደ ሥቃይ ስፍራ (ሲኦል) ይሄዳል። የሙታን ዘለቄታዊ መለየት ኢየሱስ ስለ ሀብታሙ ሰውዬና ስለ አልዓዛር በተናገረው ታሪክ ውስጥ ተገልጾአል (ሉቃ. 16:19-31)። ኢየሱስ አልዓዛር የመጽናኛ ስፍራ ወደ ሆነው የአብርሃም እቅፍ ሲወሰድ፥ ሀብታሙ ሰውዬ ወደ ሥቃይ ስፍራ እንደ ተወሰደ ገልጾአል (ሉቃ. 16:24)። ክርስቶስ ካረገበት ጊዜ አንሥቶ፥ የሚሞቱ አማኞች ሁሉ ጌታ ወዳለበት ይሄዳሉ (2 ቆሮ. 5:8)። ክርስቲያን ሲሞት

ስፍራ ተለይታ መሄድ የመጀመሪያው ሞት ነው (ራእይ 20:13)። ክርስቲያኖች ክርስቶስ ስለ ገሃነመ እሳት የተናገራቸውን ቃላት በተለያዩ መንገዶች ይተረጉማሉ። አንዳንዶች ቃል በቃል ሲተረጉሙ፥ ሌሎች ደግሞ ተምሳሌታዊ ያደርጉታል። ክርስቶስ የትኛውንም ትርጉም (ቀጥተኛ ወይም ተምሳሌታዊ) ለመስጠት ቢፈልግ፥ እውነቱ ግን ኢየሱስ ገሃነመ እሳት አስፈሪ ስፍራ እንደ ሆነ ግልጽ ማድረጉ ነው።

ከታላቁ የነጭ ዙፋን ፍርድ በፊት፥ ያልዳኑት ሙታን ፍርዳቸውን በሲኦል ሆነው ይጠባበቃሉ (ሉቃ. 16:23፤ ራእይ 20:12-13)። እንደ ክርስቶስ አገላለጽ፥ ላልዳኑት ሰዎች ሲኦልም የሥቃይ ስፍራ ነው (ሉቃ. 16:23-24)። እንደ ኢየሱስ አገላለጽ፥ እንደ አብርሃም ያሉ አምነው የሞቱ ቅዱሳን የሚጽናኑበት ሌላም ስፍራ ነበር። የብሉይ ኪዳን አማኞች ኢየሱስ በዕርገቱ ጊዜ ወደ ሰማይ እስኪወስዳቸው ድረስ፥ በሰላማዊ ስፍራ አርፈው ነበር (ኤፌ. 4:8-9)። ሲኦል (የሙታን ስፍራ) የተባለው የብሉይ ኪዳን ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ አገልግሏል።

የሚያስፈራው እውነታ ኃጢአታቸው ያልተሰረየላቸው ሰዎች ከሞት በኋላ ለዘላለም መሠቃየታቸው ነው (ማቴ. 25:41)። ሲኦል ጨለማ፥ ለቅሶና ጥርስ ማፋጨት በሚሉ ቃላት ተገልጾአል (ማቴ. 8:12፤ 22:13፤ 25:30)። ክርስቶስም ዘላለማዊ እሳት፥ ሥቃይና ቅጣት በሚሉ ቃላት ገልጾታል (ማቴ. 13:41-42፤ ማር. 9:43፤ ራእይ 14:10-11)። ኢየሱስ የሲኦል ሥቃይ ለሰው ልጆች ሳይሆን፥ ለሰይጣንና ከእርሱ ጋር ላመፁት እንደ ተዘጋጀ ገልጾአል (ማቴ. 25:41)። የሚያሳዝነው፥ ከዔድን ገነት ጀምሮ የሰው ልጆች ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ በሚያካሂደው ዓመፅ ተካፍለዋል። በኢየሱስ ክርስቶስና በመስቀል ላይ በከፈለው መሥዋዕትነት በማመን ለኃጢአታቸው ይቅርታ እስካላገኙ ድረስ፥ የሰው ልጆችም የሰይጣንን ቅጣት ይጋራሉ (ዮሐ. 8:24)።

አፍቃሪ የሆነው እግዚአብሔር ሰውን ወደ ሲኦል እንደሚልክ ለማመን የሚቸገሩ ሰዎች፥ በመጽሐፍ ቅዱስ የሲኦልን እውነትነት ከማንም በላይ የገለጸው ሁሉንም የሚያውቀው ኢየሱስ እንደ ሆነ ሊረዱ ይገባል። እግዚአብሔር ቅዱስና ጻድቅ ፈራጅ ነው። ኃጢአትን ሊታገሥ አይችልም። ለዚህም ነው በዓመፀኛ መላእክትና ሰዎች ላይ ስለ ኃጢአታቸው ሊፈረድ የሚገባው (ዕብ. 2:2)። ኢየሱስም ሰዎች ከሲኦል ሥቃይ ይድኑ ዘንድ ለኃጢአታቸው ዋጋ ለመክፈል በመስቀል ላይ

ሕይወቱን የሰጠው ለዚህ ነው። ይሁንና፥ የእርሱን ሞትና ትንሣኤ ማወቁ ብቻ አይበቃም። ወንዶችና ሴቶች ኢየሱስ ክርስቶስን ወደ ሕይወታቸው በማስገባት እንደ ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው ሊቀበሉት ይገባል (ዮሐ. 1፡12)። ይቅርታ ሊያገኙና እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ከሚያወርደው ፍርድ ሊድኑ የሚችሉት በዚህ መንገድ ነው (ማር. 1፡14-15)።

ከኃጢአታቸው ንስሐ ገብተው ክርስቶስንና ይቅርታውን ለማይቀበሉ ሰዎች፥ የሲኦል እውነታ ይጠብቃቸዋል። ይህ እውነታ ክርስቲያኖች በኢየሱስ ክርስቶስ የሚገኘውን የኃጢአት ይቅርታ ወንጌል ለማሰራጨት እንዲፈጥኑ ሊያንቀሳቅሳቸው ይገባል።

ሰ. መጽሐፍ ቅዱስ ከሙታን ጋር ስለ መነጋገር ምን ይላል?

በብዙዎቹ የአፍሪካ ማኅበረሰቦች፥ የቀብር ሥነ-ሥርዓት በጣም አስፈላጊ ክስተት ነው። ይህም የሆነው ሕያዋን ለሙታን መናፍስት ኃላፊነት እንዳላቸው የሚያመለክት ባህላዊ እምነት በመኖሩ ነው። በአንዳንድ ቡድኖች፥ አንድ ሰው ሲሞትና በተጨማሪም ከብዙ ዓመታት በኋላ ለሞተው ሰውዬ መንፈስ አስፈላጊዎቹን ግዴታዎች ለመፈጸም ዳግመኛ የቀብር ሥነ-ሥርዓት ይካሄዳል። በባህላዊ ሃይማኖቶች፥ ከሞተው ሰው መንፈስ መልእክቶችን መቀበል በጣም አስፈላጊ ነው። እግዚአብሔር ሕያዋን ከሞቱት ሰዎች ጋር ስለሚያደርጉት ግንኙነት ምን ይላል?

በመጽሐፍ ቅዱስ በሕያዋንና በሙታን መካከል እንዲደረግ የተጠቀሰ ግንኙነት የለም። እግዚአብሔር በዘዳግም 18፡10-13 ሕያዋን ከሙታን ጋር እንዳይነጋገሩ በግልጽ ይከላከላል። ሙታንን ለማነጋገር መሞከር ኃጢአት ነው።

አስቀድመን እንደ ገለጽነው፥ እግዚአብሔር ይህንን ትእዛዝ የሰጠው፥ አጋንንት የሞቱ አያት ቅድማያት በመምሰል ሰዎች ውሸትን እንዲያምኑ ሊያሳስቱአቸው እንደሚችሉና እንደሚያሳስቱአቸውም ስለሚያውቅ ነው። የሞቱ አያት ቅድማያቶቻቸው መንፈስ በመምሰል፥ አጋንንት ሰዎችን ለመቆጣጠር እንዲያመቻቸው ሊያታልሉአቸው ይችላሉ። አያት ቅድማያቶች የተወደዱና የተከበሩ በመሆናቸው፥ ሰዎች እነዚህ መናፍስት የሚነግሯቸውን ሁሉ ለማመንና ለመታዘዝ የተዘጋጁ ናቸው። ይህ ሰይጣን በዓለም ሁሉ አያሌ ሰዎችን ወደ መንፈሳዊ ሞት የነዳበት ስኬታማ ወጥመድ ነው።

በሉቃስ 16፡23-31 ሀብታሙ ሰውዬ አልዓዛር በሕይወት ለሚገኙ ወንድሞቹ ስለ ሲኦል መኖር እንዲነግራቸው ቢፈልግም፥ አብርሃም ግን የመለሰለት ከሞት በኋላ ስላለው እውነታ ለማወቅ ብሉይ ኪዳንን ሊያነቡ እንደሚችሉ ነው። አሁንም በዚህ ዘመን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ የሞትን ምሥጢራት ለማወቅ እግዚአብሔር የወሰነው ብቸኛ መንገድ ነው።

ክርስቲያን ከሙታን ጋር ስለ መነጋገር ምን ምላሽ ሊኖረው ይገባል?

ባህላዊ ሃይማኖት የሚከተሉ ሰዎች ለሞቱ ዘመዶቻቸው አክብሮት ለማሳየትና ለማስደሰት፥ መሥዋዕቶችን ያቀርባሉ። አያት ቅድማያቶች በደስታ ካልኖሩ፥ ሕያዋንን በሕመም ወይም በሌላ ዓይነት ችግር እንደሚቀጡአቸው በማሰብ ይፈራሉ። በተጨማሪም፥ በተለይ ጋብቻን ወይም ልጅ መውለድንና በሽታን ስለ መሳሰሉ የተለያዩ ጉዳዮችና ችግሮች ምን ውሳኔ እንደሚሰጡ የአያት ቅድማያቶቻቸውን ምክር ይፈልጋሉ።

እግዚአብሔር ለሕይወት ጉዳዮች ምሪት እንድናገኝ የሚፈልገው ከየት ነው? እግዚአብሔር ከሙታን ጋር የሚደረገውን ማንኛውንም ዓይነት ግንኙነት እንደሚከለክል ተመልክተናል። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «መናፍስት ጠሪዎችንና ጠንቋዮችን ጠይቁ ባሉአችሁ ጊዜ፥ ሕዝቡ ከአምላኩ መጠየቅ አይገባውምን? ወይስ ለሕያዋን ሲሉ ሙታንን ይጠይቃሉን?» ይላል (ኢሳ. 8፡19)። እግዚአብሔር፥ «መናፍስት ጠሪዎችንና (ሙታንን የሚጠሩ) ጠንቋዮችንም በሚከተል፥ በሥራቸውም በሚያመነዝር፥ በዚያ ሰው ላይ ፊቴን አከብዳለሁ፥ ከሕዝቡም መካከል ለይቼ አጠፋዋለሁ» ሲል ሕዝቡን በጥብቅ ያስጠነቅቃል (ዘሌ. 20፡6)።

እግዚአብሔር ምሪትና እርዳታ እንደሚያስፈልገን ስለሚያውቅ፥ እነዚህን ነገሮች ለማሟላት የሚያስችሉትን ሁኔታዎች አመቻችቷል። በመዝሙር (119)፡105 መዝሙረኛው፥ «ሕግህ ለእግሬ መብራት፥ ለመንገዴ ብርሃን ነው» ይላል። እግዚአብሔር ለዕለታዊ አኗኗር የምንፈልገውን ምሪት በቃሉ ውስጥ ከሚገኙ መመሪያዎች እንድናገኝ ይፈልጋል። በመዝሙር (32)፡8 እግዚአብሔር፥ «አስተምርሃለሁ በምትሄድበትም መንገድ እመራሃለሁ! ዓይኖቼን በአንተ ላይ አጠናለሁ» ሲል የተስፋ ቃል ይሰጠናል። እግዚአብሔር ይህንን ተግባር የሚያከናውነው በመጽሐፍ ቅዱስና በክርስቲያኑ ውስጥ በሚኖረው መንፈስ ቅዱስ አማካኝነት ነው።

አያት ቅድማያቶች ይሰጣሉ ስለሚባለው እርዳታ፥ የእግዚአብሔር ቃል እርዳታችን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚመጣ በግልጽ ይናገራል። የመዝሙር (121)ን ቃላት በማስተዋል አንብብ፦ «ረዳቴ ከወዴት ይምጣ? ረዳቴ ሰማይንና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም፤ የሚጠብቅህም አይተኛም . . . እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፥ ነፍስህንም ይጠብቃታል። ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም እግዚአብሔር መውጣትህንና መግባትህን ይጠብቃል» [መዝ. (121)፡1- 3፥ 7- 8]። ሰውን በችግሩ ጊዜ ሊረዳ የሚችለው ሕያው እግዚአብሔር ራሱ እንጂ አያት ቅድማያት ወይም ሌላ አይደለም። አንድ ሰው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ዕለታዊ ግንኙነት ካለው፥ የሞተ ዘመዱን ማማከር ከቶውንም አያስፈልገውም። እግዚአብሔር የምንፈልገውን እርዳታ ሁሉ ሊሰጠን ቃል ይገባልናል።

አዳዲስ ክርስቲያኖች ተገቢውን ሥነ-ሥርዓት ካልፈጸሙና ተገቢውን ትኩረት ካልሰጡ፥ የአያት ቅድማያቶቻቸውን ቁጣ ሊፈሩ ይችላሉ። እነዚህ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ክርስቶስ በምድርም ሆነ በሰማይ ሥልጣን ሁሉ እንዳለው ሊያስታውሱ ይገባል (ማቴ. 28፡18)። ክርስቲያኖች እንደ መሆናቸው፥ አሁን እግዚአብሔር አፍቃሪ አባታቸው ነው። እንዲሁም ደግሞ፥ አያት ቅድማያቶች፥ መላእክት ወይም አጋንንት ቢሆኑ፥ በአጽናፈ-ዓለሙ ሁሉ የሚገኙ መናፍስት ጌታና ንጉሥ እርሱ ነው (ዕብ. 12፡9)። እግዚአብሔር ስለሚጠብቃቸው፥ ክርስቲያኖች ከእንግዲህ ማንኛውንም ሌላ መንፈስ ወይም ሰው መፍራት አያስፈልጋቸውም [መዝ. (121)፡7- 8]። ጌታቸው ኢየሱስ ብቻ ነው።

የማንኛውንም መንፈስ ቁጣ ከፈሩ፥ ማድረግ የሚገባቸው የነገሥታት ንጉሥ የሆነው ጌታችን ይህንን መንፈስ እንዲያስወግደው መጠየቅ ብቻ ነው። ክፉ መናፍስት በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት እንደሚንቀጠቀጡ መረዳት የመንፈሳዊ ጥንካሬ ምንጭ ነው (ማቴ. 8፡29)። መዝሙረኛው፥ «እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው፤ የሚያስፈራኝ ማን ነው? እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው፤ የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?» ብሏል [መዝ. (27)፡1]።

## ሸ. በአካለ መጠን መድረሻ ባህላዊ ሥርዓቶች ላይ የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው?

በአፍሪካ ባህሎች፥ የብስለት (የአካለ መጠን) መድረሻ ሥርዓቶች ሽከልጅነት ወደ አዋቂነት መሸጋገሪያ ወሳኝ ሥርዓቶች ናቸው። ከአካለ መጠን መድረሻ ዐበይት ዓላማዎች አንዱ ለወጣቶች የፆታን ምሥጢራት፥ እርባታ፥ ጋብቻና ቤተሰባዊ ሕይወትን ማስተማር ነው። ይህ ለጋብቻና ለብስለት ዝግጅት የሚደረግ ሥርዓት ሲሆን፥ ማኅበረሰቡ በሙሉ ተካፋይ ይሆንበታል።

በአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት አማካኝነት፥ ወጣቶች በማኅበረሰባቸው ወደ አዋቂነት ሕይወት ለመግባት ተቀባይነት ያገኛሉ። ይህ ከሰውዬው የማንነት ስሜት፥ ከቤተሰቡና ከጎሳው ጋር በቅርብ የተሳሰረ በመሆኑ፥ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት በሃይማኖታዊና ባህላዊ እሳቤ የተሞላ ነው። በአፍሪካ በማኅብረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘት ከሁሉም የላቀ አስፈላጊ ነገር በመሆኑ፥ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት ተካፋይ አለመሆን ለወጣት ትልቅ ችግር ነው።

ለክርስቲያን የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች ከፍተኛ መንፈሳዊ ችግሮችን ያስከትላሉ። በመጀመሪያ፥ ሁልጊዜም ማለት ይቻላል ከአካለ መጠን መድረሻ ልምምዶች ጋር ባህላዊ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች ይኖራሉ። ስለ ሆነም፥ የዚሁ ሥርዓት ተካፋይ መሆን ለወጣት የሕዝቡን ባህሎች ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ነገሮች እንደ ተቀበለና እንዳመነባቸው ይፋዊ ምስክርነት ይሰጣል። በሁለተኛ ደረጃ፥ በሥነ-ሥርዓቱ ላይ የሚቀርቡ እሴቶችና ልምምዶች ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚቃረኑ ናቸው።

የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች ከነገድ ነገድ ይለያያሉ። አንዳንድ ጊዜ የነገዱ ወይም የጎሳው መለያ የሚሆን ምልክት በሰውነቱ ላይ ይደረጋል። አንዳንድ ጊዜ ለወንዶች ወይም ለሴቶች ልጆች ወይም ለሁለቱም የፆታዎች ግርዘት ይደረጋል። ሁልጊዜም ለማለት ይቻላል ይህ ግርዘት የሚደረገው ለጤንነት አስተማማኝ በማይሆኑ ሁኔታዎች ነው።

ክርስቲያን ወጣትና ቤተሰቡ እግዚአብሔርን የሚያስደስት ነገር አድርገው ከማኅበረሰባቸው መወገድን ቢያተርፉ፥ ወይም ክርስቲያናዊ ያልሆኑትን ተግባራት ፈጽመው ማኅበረሰባቸውን ቢያስደስቱና ከእግዚአብሔር ዘንድ ፍርድ ቢቀበሉ እንደሚሻል በማሰብ ያመነታሉ። በጎሳው ውስጥ ተቀባይነት ለማግኘት ተገቢውን ማካካሻ እስካላደረገ

ድረስ፥ ለአካለ መጠን ሥርዓት የሚቀርብ ማንኛውም መፍትሔ ውጤታማ ሊሆን አይችልም።

## የሴት ልጅ ግርዘት እንደ አካለ መጠን መድረሻ

በብዙ የአፍሪካ ክፍሎች የሴት ግርዘት ለልጃገረዶች የሚደረግ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት አካል ነው። ለክርስቲያኖች ይህ ልምምድ ከፍተኛ ችግሮችን ስለሚያስከትል፥ በዚህና ባጠቃላይም በግርዘት ላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አመለካከትን እናቀርባለን። የሴት ግርዘት ለአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት አስፈላጊ ልምምድ መሆኑን የሚጠቁሙ አያሌ ባህላዊ ምክንያቶች ተሰጥተዋል።

1. ብዙውን ጊዜ ለሴት ግርዘት የሚቀርበው ምክንያት የሴቲቱን ወሲባዊ ፍላጎት በመገደብ ለባሏ ታማኝ ያደርጋታል የሚል ነው። ከተገረዘች፥ ካገባች በኋላ ከሌሎች ጋር ዝሙት እንደማትፈጽም ይታመናል። ከክርስትና አንጻር፥ ለዚህ አመለካከት ሁለት ከፍተኛ ተቃውሞዎች አሉ።

በመጀመሪያ፥ በከፍተኛ ወሲባዊ ፍላጎት የሚሠቃዩት ወንዶች እንጂ ሴቶች እንዳልሆኑ ማንም ሰው ያውቃል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንዲገረዙ የታዘዙት ወንዶች ብቻ እንጂ ሴቶች አለመሆናቸው ለዚህ አንደኛው ምክንያት ሊሆን ይችላል። ሁለተኛ፥ በብዙ ነገዶች ለሴቶችና ለወንዶች ሚዛናዊ ያልሆነ እጥፍ የግብረ-ገብ መመዘኛ አለ። ወንዶች ባሻቸው ጊዜ ተጨማሪ የወሲብ ጓደኞችን ሲፈልጉ በዝሙታ እየታለፈ፥ ከሴቶች ከብረ-ንጽሕናና ታማኝነት መፈለጉ አግባብ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር የዝሙት ኃጢአቶችንና ወሲባዊ ግድፈትን በተመለከተ በወንድና ሴት መካከል ገደብ አያበጅም (ዘጸ. 20፡14፤ ዕብ. 13፡4)። እነዚህ ለወንዶችም ለሴቶችም ኃጢአት ናቸው። ይህ በሴቶች ላይ የተጣለ ድርብርብ መመዘኛ የራስን ምኞት ለማርካት በወንዶች የኃጢአት ልብ የተዘጋጀ ነው።

2. የሴት ግርዘት በጎሳዋ አዋቂዎች ዓይን ልጃገረድን ከልጅነት ወደ ሴት አዋቂነትና ብስለት የሚያሸጋግር አስፈላጊ ደረጃ ተደርጎ ይቆጠራል። ይህም ልምምድ የሚቀጥለው፥ በጎሳው አባላት የአዋቂነትን ተቀባይነት ማግኘቱ ዋንኛ ነገር በመሆኑ ነው። በባህሉ ተቀባይነት ማግኘት አስፈላጊ ሊመስል ይችላል። ይሁንና፥ እግዚአብሔር ሰዎችን በኢየሱስ ክርስቶስ በማመናቸው ሁኔታ እንዲሁ እንደሚቀበል ልብ ልንል ይገባል።

3. ሌላው የቤት ግርዘት ጠቀሜታ፥ ከትክክለኛው የግርዘት ሥርዓት ቀደም ብሎና ቀጥሎ በሚመጡ ሳምንታት ወይም ወራት ውስጥ አስፈላጊው ትምህርትና ሥልጠና መሰጠቱ ነው። ይህም ትምህርት በጋብቻ፥ በፆታዊ ግንኙነቶች፥ ልጅ በመውለድና በቤተሰብ ሕይወት የአዋቂዎችን ኃላፊነቶች የሚጨምር ነው። በዚህ የትምህርት ጊዜ ጎሳዊ እሴቶች፥ ወጎችና እምነቶች ላይ ትኩረት ይደረጋል።

ለወጣቶች የብስለትን ሕይወት በተመለከተ ባህላዊ ትምህርት መስጠቱ አስፈላጊ ነው። ይሁንና፥ አንድ ክርስቲያን ወጣት መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ልጆች ሁሉ ለጋብቻና ለቤተሰብ ጉዳዮች የሚያስፈልጉትን መለኮታዊ መመዘኛዎች እንደሚያስተምር ሊረዳ ይገባዋል። ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር መመዘኛዎች ከጎሳዊ ባህሎች የተለዩ ናቸው። ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን ለማስደሰትና በሕይወታቸውም የእርሱን በረከት ለመቀደስ ከፈለጉ፥ የእግዚአብሔርን መመዘኛዎች መከተል አለባቸው።

አንዳንድ ባህላዊ ልምምዶች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጋጩባቸው ጊዜያት አሉ። የዚህ ዓይነት ግጭት በሚኖርበት ጊዜ፥ ክርስትያን የመጽሐፍ ቅዱስን ትምህርት መታዘዝ አለበት። ይህ ግን አስቸጋሪና ከጎሳው ዘንድ ተቀባይነት ማጣትንና ስደትን ሊያስከትል ይችላል። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ውስጥ፥ ክርስቲያኖች በሕይወት ውስጥ ከሁሉም የሚልቀው ምን እንደ ሆነ ራሳቸውን መጠየቅ አለባቸው። ለዚህች አጭር ሕይወት ብለው የባህላቸውን ሕዝቦች ሊያስደስቱና የእግዚአብሔርን ኩነኔና ፍርድ ሊቀበሉ ነው? ወይስ እግዚአብሔርን በማስደሰት፥ በዚህ ዓለምም ሆነ በዘላለሙ መንግሥት በሕይወታቸው የእግዚአብሔርን በረከት ሊቀበሉ ነው?

ከብዙ ጊዜያት በፊት፥ ኢያሱና የእስራኤል ሕዝብ በዙሪያቸው የሚገኙትን ባህላዊ ሕዝቦች ልምምዶች ወይም እግዚአብሔርን ከመከተል አንዱን መምረጥ ነበረባቸው። የኢያሱ ምላሽ ምን ነበር? ኢያሱ፥ «እግዚአብሔርንም ማምለክ ክፉ መስሎ ቢታያችሁ፥ አባቶቻችሁ በወንዝ ማዶ ሳሉ ያመለኩአቸውን አማልክት ወይም በምድራቸው ያላችሁባቸውን የአሞራውያንን አማልክት ታመልኩ እንደ ሆነ፥ የምታመልኩትን ዛሬ ምረጡ። እኔና ቤቴ ግን እግዚአብሔርን እናመልካለን» ብሏል (ኢያሱ 24:15)። ኢያሱ እግዚአብሔርን ለማምለክና ለማገልገል በመምረጡ፥ እግዚአብሔር ለዚህ አቋሙ አትረፍርፎ ባርኮታል።

4. ወደ አዋቂው የጎሳው ኅብረተሰብ ተቀባይነት ከማግኘቱ ጋር፥ ከሞቱትና በሕይወት ካሉ ከጠቅላላዎቹ ጎሳዎች ጋር የመደባለቁም ጉዳይ አለ። በግርዘት ወይም በሌሎች የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች ላይ ደም መርጨት፥ ብዙውን ጊዜ ወንዱን ወይም ሴቷን ልጅ በቃል ኪዳን ከጎሳው ጋር ለማዋሃድ ታስቦ የሚደረግ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ የሆነ በደም የሚፈጸም ቃል ኪዳን ያስተምራል። እግዚአብሔር ለአብርሃም የግርዘት ደም እግዚአብሔር የመረጣቸው ሰዎች በደም ቃል ኪዳን ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ተዋሃዱ የሚያመለክት ተምሳሌት እንደ ሆነ ነግሮታል። እግዚአብሔር፥ «ቃል ኪዳኔንም በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ ከዘርህ ጋር በትውልዳቸው ለዘላለም ኪዳን አቆማለሁ፥ ለአንተና ከአንተ በኋላ ለዘርህ አምላክ እሆን ዘንድ» ብሏል (ዘፍጥ. 17፡7)። በመቀጠልም፥ «በእኔና በአንተ መካከል ከአንተም በኋላ በዘርህ መካከል የምትጠብቁት ቃል ኪዳኔ ይህ ነው፤ ከእናንተ ወንድ ሁሉ ይገረዝ። የቁልፈታችሁንም ሥጋ ትገረዛላችሁ፤ በእኔና በእናንተ መካከል ላለውም ቃል ኪዳን ምልክት ይሆናል» ብሏል (ዘፍጥ. 17፡10-11)።

የደም ቃል ኪዳን ጉዳይ በባህላዊ ግርዘትና መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግርዘት በሚያስተምረው አሳብ መካከል ግልጽ ልዩነት ያመጣል። ዋናው ጥያቄ በቃል ኪዳን የምንዋሃደው ከማን ጋር ነው? የሚለው ነው። የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓት ግርዘትን ወይም ሌላ ከንውን ቢያካትት፥ ይህ እውነት ነው። እግዚአብሔር ለእርሱ ያለንን ታማኝነት የሚተካ ማናቸውንም ዓይነት ሌላ ቃል ኪዳን እንድናደርግ አይፈልግም። አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ሳይሆን፥ ከአያት ቅድማያት ጋር የሚያዋህደው የደም ቃል ኪዳን በመፈጸሙ፣ የመጀመሪያውን ትእዛዝ ይተላለፋል (ዘጸ. 20፡3)።

ክርስቲያኖች እንደ መሆናችን፥ በራሳችን ደም ሳይሆን ራሱ ባፈሰሰልን ደም ከጌታችንና ከመድኃኒታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር በደም ቃል ኪዳን ተዋህደናል (ራእይ 5፡9)። የወደደንና ከኃጢአታችን በደሙ ያጠበን ኢየሱስ ነው (ራእይ 1፡5)።

**መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ግርዘት የሚሰጠው አጠቃላይ ትምህርት**

1. እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን ውስጥ እንዳዘዘው፥ ግርዘት ለወንዶች ብቻ የተሰጠ ሥርዓት ነው። እግዚአብሔር ሴቶች እንዲገረዙ ያዘዘበት ስፍራ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አይገኝም (ዘፍጥ. 17፡10)።

2. የብሉይ ኪዳን ግርዘት በእግዚአብሔር እና በሰዎች እንጂ በሰዎችና በሰዎች መካከል የሚደረግ የቃል ኪዳን ምልክት አልነበረም (ዘፍጥ. 17፡11)። ይህም የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ከራሱ ጋር በልዩ ግንኙነት ለመመሥረት የታሰበ ቃል ኪዳን ነው (ዘፍጥ. 17፡7)። ስለ ሆነም፥ ይህንኑ ተምሳሌት በጎሳዎች መካከል የሚከናወን ቃል ኪዳን አድርጎ መውሰዱ፥ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተሰጠውን የግርዘትን ዓላማ መቀልበስ ነው።

3. የብሉይ ኪዳን ግርዘት ለአካለ መጠን ሲደርሱ ሳይሆን፥ በስምንተኛው የልደት ቀን የሚከናወን ነበር (ዘፍጥ. 17፡12፤ ዘሌ. 12፡3)። በእግዚአብሔር ዕቅድ፥ ከጉርምስናና የአዋቂነት ሥልጠና ጋር የሚያገናኘው ነገር አልነበረም። የሚገረዙት ገና የተወለዱ ሕፃናት በመሆናቸው፥ የሕመም ትውስታ አይኖርም ነበር።

4. በመጽሐፍ ቅዱስ የግርዘት ፍች የሕይወትን ቅድስና የሚያስከትል ግላዊ የቃል ኪዳን ግንኙነትን ያካትታል። «የልብ ግርዘት» ማለትም ይኸው ነው (ዘዳ. 30፡6፤ ቆላ. 2፡11)። ይህም ከጌታ ጋር በልብና በነፍስ ከመዋሃድ የሚገኝ ነው። ስለ ሆነም፥ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው ግርዘት ሥጋዊ ሳይሆን መንፈሳዊ ነው። ይህ መንፈሳዊ ፍች ሥጋዊ ግርዘት በተጠየቀበት አዲስ ኪዳን ሳይቀር ተገልጾአል (ዘዳ. 10፡16፤ 30፡6፤ ኤር. 4፡4፤ 9፡26)።

5. የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የመጀመሪያው ጉባኤ የተጠራው በአዲስ ኪዳን ዘመን ለመዳን ሰዎች የሥጋ ግርዘት ይፈጽሙ ዘንድ ይገባቸው እንደ ሆነ ለመወሰን ነበር (የሐዋ. 15፡1-6)። የዚህ አስቸጋሪና ረዥም ጉባኤ ውጤት፥ ሥጋዊ ግርዘት የእግዚአብሔር የቃል ኪዳን ሕዝብነት ምልክትነቱ ለዘላለም እንደ ቀረ የሚያመለክት ነበር (የሐዋ. 15፡8-10፥ 23-29)።

በኋላም ጳውሎስ እጅግ የሚያስፈልገው የልብ መንፈሳዊ ግርዘት ሲሆን (ቆላ. 2፡11-13)፥ ሥጋዊ ግርዘት ዛሬ ምንም መንፈሳዊ ጠቀሜታ እንደሌለው ገልጾአል (1 ቆሮ. 7፡19)። ዛሬ ክርስቲያን ወንዶች በሥጋ

ውስጥ መንፈሱ እንዲሰፍር የሚደረገው በመድኃኒት አዋቂ፥ በደብተራ ወይም በጠንቋይ አማካኝነት ነው። ድግምቶች አካላዊ ህልውና የሌላቸው ተደርገው ሲቆጠሩ፥ በአንገት ላይ የሚንጠለጠሉ ክታቦች ግን በውስጣቸው ከሚኖረው መንፈስ የተነሣ አካላዊ ህልውና እንዳላቸው ይታመናል።

ምትሐት ሰፊ የምሥጢራዊ አጠቃቀሞችን ሁኔታ ሊያመለክት ይችላል። የመድኃኒት አዋቂዎች፣ ጠንቋዮች፣ ዝናብ አውራጆች፥ ደብተሮች፥ አስማተኞችና ተራ ሕዝቦች የምትሐትን ተግባር ሊያከናውኑ ይችላሉ። ጥቁር (አደገኛ) ምትሐት፣ ነጭ (ጠቃሚ) ምትሐት፣ በሰውነት ንኪ.ኪ. (በመተላለፍ) የሚሠራ ምትሐትና በተመሳሳይነት ሕጎች የሚሠራ ("homeopathic") ምትሐት እንዳለ ይታመናል። ስለ መድኃኒትና ምትሐት ኃይል የሚናገሩ ታሪኮች በአፍሪካ አያሌዎች ናቸው። ስለ ተለያዩ የመድኃኒት ዓይነቶች፥ ምትሐት፣ ክታቦች፣ ድግምቶች፥ የእርግማንና በመሬት ላይ የሚጣሉ መድኃኒቶች ኃይል ብዙ ይነገራል። በኢትዮጵያ ስለሚገኘው ተላላፊ ምትሐት የሚያሳየው ቀጣዩ እውነተኛ ታሪክ፥ በሺህ ከሚቆጠሩ ተመሳሳይ ታሪኮች አንዱ ነው፡-

አንድ ወጣት በአንዲት ልጃገረድ ፍቅር ሲታጠል እርሷ ግን አትወደውም ነበር። ወጣቱም ወደ አንድ አስማተኛ ጎራ ብሎ የልጅቷን ፍቅር የሚያገኝበትን መላ ጠየቀው። አስማተኛውም የልጅቱን ደብተር እንዲያመጣለት ጠየቀው። ደብተሩንም ባመጣለት ጊዜ አስማተኛው በደብተሩ ላይ ከምትሐት መጻሕፍት ጥቅሶችን በቀይ ቀለም ጻፈ። ከዚህ በኋላ ልጅቱ በሚያስገርም ሁኔታ ወደ ልጁ በፍቅር ተሳበች። ሌላ የትኛዋም ልጃገረድ እንድትቀርበው አትፈልግም ነበር።

በኋላም ልጁ ሞተ! ልጂቱ ግን የልጁን መሞት ቶሎ አልሰማችም ነበር። የልጁን ሞት እስከትሰማ ድረስ፥ በከፋ መናፍስት ትሠቃይ ነበር። የልጁን መሞት እንደ ሰማች፥ መናፍስቱ ጥለዋት ሄዱ።

የመድኃኒትና የምትሐት ኃይል የሚመጣው ከየት ነው? እንደ ምትሐታዊና ምሥጢራዊ ኃይላት ላለው ሰፊ ርዕሰ-ጉዳይ ሁሉንም አስተያየት ማስተናገድ ይቻላል። በሌላ በኩል፥ ብዙ ጊዜ ምትሐት ነው ተብሎ የታመነው ነገር ብልሃት የታከለበት ማታለያ ከመሆን አላለፈም። ይህም ሆኖ፥ በታመኑ ምስክሮች የተረጋገጡ ብዙ የመንፈሳዊ ምትሐት ኃይላት ታይተዋል። በእነዚህ ሁለት እውነታዎች መካከል መድኃኒት፥ ምትሐት፥ ድግምት፥ እርግማንና ሌሎችም ስያሜዎች የተሰጡአቸውና ለማብራራት የማይሞከሩ የአያሌ ክስተቶች ምሳሌዎች ታይተዋል።

መጽሐፍ ቅዱስ እንደዚህ ስላሉ ኃይላት ምን ይላል? እግዚአብሔር በእነርሱ መገልገልን ይደግፋል? የመጽሐፍ ቅዱስ አመለካከት ምንድን ነው?

መጽሐፍ ቅዱስ በምትሐት አጠቃቀም ውስጥ የመንፈሳዊ ኃይልን መኖር ያረጋግጣል (ዘጸ. 7፡11-12፤ ዘዳ. 18፡10-12)፤ ይሁንና፥ እግዚአብሔር በእነዚህ ኃይላት መጠቀምን ይኮንናል (ዘዳ. 18፡10)። የሚጠቀሙባቸውንም ሰዎች ይኮንናል (ዘጸ. 22፡18፤ ኤር. 27፡9-10)። በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ፥ እግዚአብሔር አንድ ሰው ሌሎችን ሰዎች ወይም ሁኔታዎች ለመቆጣጠር ወይም በመማሪያነት ለመገልገል በምሥጢራዊ ኃይላት መጠቀሙን ይኮንናል። ይህም ክርስቲያን ያልሆኑትን የብዙ ሰዎች (ምሳሌ 28፡9፤ ኢሳ. 1፡15) እና አንዳንድ ጊዜም፥ ክርስቲያኖች ነን የሚሉትንም ወገኖች ጸሎት ይጨምራል (ያዕ. 4፡3)። እግዚአብሔር የሚደግፈው ጸሎት፥ ከቶውንም የራሳችንን ፈቃድ ለማድረግ ሰዎችን በብልሃት ለመቆጣጠር ወይም እግዚአብሔርን በኃይል ለማስገደድ መሞከር አይደለም። ይልቁንም፥ እውነተኛ ጸሎት የእግዚአብሔር ፈቃድ በሰዎች ጉዳዮች ውስጥ እንዲፈጸም ከእግዚአብሔር ጋር መተባበር ነው። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱ፥ «መንግሥትህ ትምጣ፥ ፈቃድህ በሰማይ እንደ ሆነች እንዲሁ በምድር ትሁን» ብለው እንዲጸልዩ አስተምሮአቸዋል (ማቴ. 6፡10)።

በምትሐት፥ በመድኃኒት፥ በድግምት፥ በእርግማን፥ በክታብና በሌሎችም ተጽዕኖዎች መንፈሳዊ ኃይል በሚገለጽባቸው ሁኔታዎች፥ የኃይሉ ምንጭ እግዚአብሔር ሳይሆን፥ ሰይጣንና አጋንንቱ ናቸው። አጋንንት በኃጢአት ለሚመላለሱና ሌሎችን ሰዎች ለመቆጣጠር ወይም ራሳቸውን ለመጠበቅ ምሥጢራዊ ኃይሉ ለሚሹ ሰዎች ኃይላቸውን ለማጋራት ከፍተኛ ፍላጎት አላቸው።

ሰዎች ምትሐት፥ ባህላዊ መድኃኒት፥ ድግምትና ሌሎችንም ተመሳሳይ ተግባራት ሲፈጽሙ፥ ምንም እንኳ ዓላማቸው መልካም ሊመስል ቢችልም የአጋንንትን ኃይልና ሥራ እያከናወኑ ናቸው ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ፥ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሁልጊዜም ምትሐታዊ ኃይል ከሚጠቀሙ ሰዎች ጋር በመጋጨትና ተቃውሞ በማሳየት አሳልፈዋል። ሙሴ የግብፅን አስማተኞች ሲቃወም (ዘጸ. 7፡10-12)፥ ጴጥሮስ ደግሞ ስምዖን የተባለውን የሰማርያ አስማተኛ ተቃውሞአል (የሐዋ. 8፡18-23)።

በምትሐት አጠቃቀም ውስጥ ሁለት መሠረታዊ ችግሮች አሉ። በመጀመሪያ፥ እውነተኛ ጸሎት የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዲፈጸም ሲሻ፥ ምትሐት ግን የምትሐተኛው ሰው ፈቃድ እንዲፈጸም ይፈልጋል። ምትሐት በራስ-ወዳድነትና የምትሐተኛውን ፈቃድ በመፈጸሙ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ነው። ሁለተኛ፥ ምትሐቱን የሚጠቀመው ሰው እግዚአብሔርን በመታመን የምትሐቱን ውጤት ለመተው አይፈልግም። ይልቁንም፥ ምትሐት የሚጠቀመው ሰው በምሥጢራዊ ኃይል የራሱን ፈቃድ ለመፈጸም ይወስናል። ስለ ሆነም፥ ምትሐት በትክክል ኃጢአትና በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም ግልጽ ዓመፅ ነው።

በመጀመሪያ በእግዚአብሔር ላይ ያመፀው ሰይጣን ስለ ሆነ፥ በምትሐት አማካኝነት ምኞታቸውን ለማሟላት ለሚሹ ሰዎች በአጋንንቱ በኩል መንፈሳዊ ኃይል ለመስጠት ከፍተኛ ፍላጎት አለው። ነገሩ መልካም (ነጭ) ወይም ክፉ (ጥቁር) ምትሐት ሊመስል ቢችልም ይህ እውነት ነው። በዘዳግም 18፡10-12 እግዚአብሔር፥ «ምዋርተኛም፥ ሞራ ገላጭም፥ አስማተኛም፥ መተተኛም፥ በድግምት የሚጠነቁልም፥ መናፍስትንም የሚጠራ፥ ጠንቋይም፥ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህን የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው» ይላል።

እግዚአብሔር እነዚህን ልምምዶች የኮነነበት ምክንያት ከሙታን ጋር መነጋገርን ከኮነነበት ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው። ይህ ኃጢአት ነው። ሰዎችን ወደ ሰይጣን ወጥመድ፥ በዚያውም ወደ መንፈሳዊ ሞት ይመራል (ዘዳ. 32፡16-18፤ 1 ቆር. 10፡20-22)። አንዳንድ ደካማ የአፍሪካ ክርስቲያኖች አሁንም ምትሐት ወይም ክታቦችን ይጠቀማሉ። ይህም በችግራቸው ጊዜ ከእግዚአብሔር የተለየ አካል እንዲረዳቸው የሚፈልጉ መሆናቸውን ይገልጻል። በእግዚአብሔር አለመተማመናቸውን ያሳያል። እግዚአብሔር በርሱና በርሱ ብቻ እንድንተማመን ይፈልጋል። መዝሙር (40)፡4፥ «እግዚአብሔርን የታመነ . . . ወደ ሐሰተኛ ያልተመለከተ ሰው ምስጉን ነው» ይላል። መዝሙር 62፡8ም፥ «የሕዝብ ማኅበር ሁላችሁ፥ በእርሱ ታመኑ» ሲል፥ ምሳሌ 29፡25 ደግሞ፥ «በእግዚአብሔር የሚታመን ግን እርሱ ይጠበቃል» ይላል።

ኢየሱስን ጌታቸውና አዳኛቸው አድርገው የማያምኑ ሰዎች፥ በሚያታልሉ መናፍስት መንፈሳዊና ሥጋዊ ጥቃቶች እንደሚደርሱባቸው መገንዘብ አስፈሪ አሳብ ነው። ባህላዊ ልምምዶችን የሚከተሉ ሰዎች መድኃኒቶችና ምትሐቶች ከክፉ መናፍስትና ከጠንቋዮች ኃይላት

ሊከዱና ሊያወግዙ ይገባል። እንደ እግዚአብሔር ቃል አገላለጽ፥ የአያት ቅድማያት ኃጢአቶች በኋለኞቹ ትውልዶች ላይ ይመጣሉ (ዘጸ. 20:5፤ 34:7፤ ዘዳ. 5:9)። ሰይጣንም ይህንን ስለሚያውቅ፥ የሕዝቦችን ትውልዶች ለማጥቃት ይጠቀምበታል። ለክርስቲያን ሰይጣን በአያት ቅድማያቶቹ ላይ የነበረውን ቁጥጥር፥ በአንደበቱ ማውገዝና በኢየሱስ ስምና በደሙ ኃይል መተማመን አስፈላጊ ነው።

በሙሴ ሕግ ውስጥ እግዚአብሔር ወቅታዊ ፍርድና ሥቃይ ከቀድሞው ትውልዶች ኃጢአት ጋር ስለሚገናኙባቸው አንዳንድ ገጠመኞች ተናግሯል፤ እግዚአብሔር፥ «ከእናንተም ተለይተው የቀሩት በጠላቶቻቸው ምድር ላይ በኃጢአታቸው ይከሳሉ፤ በአባቶቻቸውም ኃጢአት ደግሞ ከእነርሱ ጋር ይከሳሉ። . . . ኃጢአታቸውንም የአባቶቻቸውንም ኃጢአት ይናዘዛሉ . . . በዚያን ጊዜ ያልተገረዘው ልባቸው ቢዋረድ፥ የኃጢአታቸውንም ቅጣት ቢቀበሉ፥ እኔ ለያዕቆብ የማልሁትን ቃል ኪዳኔን አስባለሁ፤ ደግሞ ለይስሐቅና ለአብርሃም የማልሁትን ቃል ኪዳን አስባለሁ፤ ምድሪቱንም አስባለሁ» ብሏል (ዘሌ. 26:39-42)።

ክርስቲያኑን ከሰይጣን ኃይል የሚጠብቀው እግዚአብሔር እንጂ የምትሐት ኃይል አይደለም (ኤፌ. 6:10-11)። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዛቸዋልና» ይላል [መዝ. (91):11]። ክርስቲያን ራሱን ከክፉ መናፍስት ለመከላከል እንደ እምነት፥ ጸሎትና የእግዚአብሔር ቃል ያሉትን መንፈሳዊ የጦር ዕቃዎች እንዲያነሣ ተመክሯል (ኤፌ. 6:12-18)።

### በ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ምዋርተኛነት ምን ይላል?

በአፍሪካ፥ ምዋርት አንድን ሰው ለሕመም፥ ለችግሮች ወይም ለሞት የዳረገውን ሰው ለመለየት የሚጠቀሙበት የተለመደ ዘዴ ነው። ሰው ማንን እንደሚያገባ፥ የተወሰኑ እህሎችን መቼ እንደሚዘሩ፥ ወይም አንድን ጉዞ መቼ እንደሚያደርግ፥ ወዘተ. ለመወሰን ወይም ምክር ለማግኘት የሚጠቀሙበት ነው። አያት ቅድማያቶችን ስላስቀየሙበት ሁኔታ ተረድተው መፍትሔ ለመሻትም ይገለገሉበታል። ሰዎች የትኛው ሥርዓት ወይም መሥዋዕት አንድን ችግር እንደሚፈታ ለማወቅ በምዋርት ይጠቀማሉ። አንዳንድ ጊዜ ጠላትን ለመበቀል ይፈልጋሉ። ምዋርት የወደፊቱንም ለመተንበይ ይረዳል። እንደዚሁም በእግዚአብሔር ላይ ሳይደገፉ ስለ አንድ ሁኔታ እውቀት ወይም ምክር ለማግኘት

ሲጠቀሙበት፥ የዚህ ኃይል ባለቤቶች ግን እግዚአብሔር ይህንን ኃይል እንደ ሰጣቸው ይናገራሉ (ሕዝ. 13፡6፥ 9)።

ምዋርት፥ ጠጠር በመጣል፥ የእንስሳትን አካላት በማየት፥ የትናንሽ ጭራሮዎችን ወይም በመሬት ላይ የወደቁትን የሸክላ ስብርባሪዎች በመመልከት፥ በተወሰኑ ምሥጢራዊ ዕቃዎች ላይ በትር እንዲወዛወዝ በማድረግ፥ ሕልሞችንና ራእዮችን በመተርጎም፥ ጣቶችን በመንካት፥ የእጅ መዳፎችን በመመርመር፥ ካርታ ወይም ሌሎች ነገሮች በማየት፥ የሻይ ወይም የቡና ጭላጭ መስመሮችን በማንበብና በሌሎችም አያሌ መንገዶች ሊከናወን ይችላል። ምዋርት ከመናፍስት ጋር በመነጋገር ከመናፍስት ዓለም ምሥጢራዊ መረጃ ተቀብሎ ለሚያማክረው ሰው ችግር መፍትሔ የሚሰጠው ነው።

እንደ አንዳንድ ምትሐትና የመንፈስ መጠመድ፥ ብዙው የምዋርት ሥራም ከማታለያ ጨዋታ ያለፈ አይደለም። አንድ ብልህ ሽማግሌ ሕዝቡን በሚገባ ስለሚያውቅ፥ ከአያት ከቅድማያት መንፈስ እንደ ተነገረ በማስመሰል በጣም የተገናዘበ ምክር ሊሰጥ ይችላል። ግንኙነታቸውን፥ ምቀኝነታቸውን፥ ጥላቻቸውን፥ ጭንቀቶቻቸውን፥ የአመለካከት ችግሮቻቸውንና እርስ በርሳቸው የሚያጋጥሙአቸውን እክሎች ስለሚያውቅ፥ ባህሉ በሚቀበለው መንገድ መፍትሔዎችን ያቀርባል። ምናልባትም አብዛኛዎቹ የአፍሪካ ጠንቋዮች በዚህ መንገድ የሚሠሩ ናቸው።

በማኅበረሰቡ ውስጥ የምዋርትን ተግባር ከሚያከናውነው ብልህ ሽማግሌ በተጨማሪ፥ ከራሳቸው ግንዛቤና ፍርድ በላይ በትክክል ከመንፈሳዊ ኃይላት ምሥጢራዊ እውቀት የሚቀበሉ ግለሰቦች አሉ። መጽሐፍ ቅዱስ የዚህ ዓይነቱ ርኩሰት እንዳለ በመግለጽ (ዘዳ. 18፡10)፥ ለምሥጢራዊው እውቀት ምንጩ የምዋርት መንፈስ ማለትም አጋንንት እንደ ሆነ ያመለክታል። ጳውሎስ በፊልጵስዩስ ይኸው ኃይል ከነበራት ሴት ጋር ካደረገው የኃይል ተግዳሮት ታሪክ፥ ኃይሉ የመጣው በሴቲቱ ውስጥ ከነበረው መንፈስ እንደነበር እንረዳለን (የሐዋ. 16፡16-19)። በዚህ ታሪክ ውስጥ የተጠቀሰችው ሴት የምዋርተኝነት ኃይል የነበራት ሲሆን፥ የተወሰኑ ሰዎች በኃይሏ ገንዘብ ለማከማቸት ችለው ነበር። እንዲህ ዓይነቶቹ ሰዎች የወደፊት ክስተቶችን በትክክል ሊተነብዩ ወይም ሌሎች የምሥጢራዊ ኃይል መግለጫዎችን ሊያሳዩ ይችላሉ። ጳውሎስ ከሴቲቱ

መንፈሱን ባስወጣው ጊዜ፥ ሴቲቱ የምዋርተኝነት ኃይሏን አጣች፤ ጌቶቿም የገንዘብ ምንጫቸው በመድረቁ በጣም ተቆጡ (የሐዋ. 16፥18-19)።

## እግዚአብሔር ምዋርተኛነት የሚኮንነው ለምንድን ነው?

በዘዳግም 18፥10-12 ጌታ፥ «ምዋርተኛ፥ ሞራ ገላጭም . . . በአንተ ዘንድ አይገኝ። ይህንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው» ይላል። በዘሌዋውያን 19፥26 ጌታ፥ «አስማትም አታድርጉ፥ ሞራ ገላጭም አትሁኑ» ይላል። እግዚአብሔር ምዋርትን የሚኮንንበት ምክንያት ምትሐትንና ከሙታን ጋር መነጋገርን ከሚኮንንበት ጋር በጣም ተመሳሳይ ነው። እንደ ሌሎቹ ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ሃይማኖቶች ልምምዶች ሁሉ፥ ምዋርተኝነት ሰው ከሕያው እግዚአብሔር ይልቅ በሌላ ነገር ወይም ሰው እንደሚታመን ይገልጻል። ሰዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ በሌላ ሰው ወይም ነገር ሲታመኑ፥ የመጀመሪያውን ትእዛዝ በመጣስ ኃጢአት ይፈጽማሉ (ዘዳ. 5፥7)። እንዲሁም፥ ራሳቸውን ለአጋንንታዊ መታለልና ተጽዕኖ ያጋልጣሉ።

ልምምዱ ክፉት ስለማይመስል፥ ክርስቲያኖችን ጨምሮ ብዙ ሰዎች በምዋርት ይታለላሉ። ሰዎች እንዲህ ዓይነት ኃይል ያላቸውን ግለሰቦች መልካም አድራጊዎችና ሌሎችን ረጂዎች አድርገው ይመለከቱአቸዋል። ለተመሳሳይ ምክንያቶች ኃጢአተኛውን ወይም ጠንቋዩን የማኅበረሰቡ ወዳጅ አድርገው ያዩታል! በአንዳንድ ስፍራዎች አንድ ሰው ምዋርተኛና መድኃኒተኛ በመሆን ይሠራል። የማኅበረሰቡ አባላት በሽታ ወይም ችግር ያስከተለባቸውን ሰው ማወቁ ምን ጥፋት እንዳለው ሊጠይቁ ይችላሉ።

ከሰይጣን እንደሚመጡ ሌሎች ኃይላት ሁሉ፥ ትክክለኛው የምዋርተኝነት መንፈስ በሚሠራበት ጊዜ በተዘዋዋሪ መንገድ የሚከናወን መታለል አለ። ሰዎች የተንባይን ወይም የጠንቋይን ቃል ወደ ማመኑ ያዘነብላሉ። ይሁንና፥ የጠንቋዩን ቃላት እውነተኛነት እንዴት ያውቃሉ? ኢየሱስ ሰይጣን ውሸተኛና የውሸትም አባት እንደ ሆነ ተናግሯል (ዮሐ. 8፥44)። ትክክለኛ የምዋርተኝነት ኃይል ያላቸው ሰዎች ኃይሉን የተቀበሉት ከዚህ መንፈስ እንደ መሆኑ፥ የምዋርተኛውን ቃላት የሚያምኑ ሰዎች በአጋንንት ውሸት መታለላቸው አይቀርም።

ብዙውን ጊዜ ምዋርት የበሽታን ወይም የመጥፎ ገጠመኝን ምክንያት በሌላ ሰው ወይም በአያት ቅድማያት ላይ ያላክካል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን የችግሮቻችንን መንስዔ እኛው በእግዚአብሔር ላይ በፈጸምነው ኃጢአትና

ዓመፀኛነት ላይ ያሳርፋል (ያዕ. 5፥16)። ብዙውን ጊዜ የምዋርተኝነት ችግሮቻችን የሚመነጩት ከአያት ቅድማያት መቀየምና ቅጣት እንደ ሆነ ይገመታል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሕዝቡን የሚቀጣው እግዚአብሔር እንጂ አያት ቅድማያቶች እንዳልሆኑ ይገልጻል (ዕብ. 12፥6)። ስለ ሆነም፥ ክርስቲያኖች አያት ቅድማያቶቻቸውን ሳይሆን እግዚአብሔርን እንዳያሳዝኑ ሊጠነቀቁ ይገባል።

በተጨማሪም፥ ጠንቋዩ ተጻራሪው በሆነ ሌላ ጠንቋይ ወይም አስማተኛ ላይ ለምን ተፈታተነኝ በማለት የበቀል እርምጃ ወደ መውሰዱ ያመራል። በአንድ ሰው እርግማን ያወረደውን ሰው ከእግዚአብሔር በቀር ማን ሊያውቀው ይችላል! ጠንቋዩ ግን ራሱን በእግዚአብሔር ዙፋን ላይ በማስቀመጥ ታላቅ ኃጢአት ይፈጽማል። በተጨማሪም፥ በቀል የእግዚአብሔር በመሆኑ፥ በቀልን እንዳንመልስ መጽሐፍ ቅዱስ በጥብቅ ያስጠነቅቀናል (ሮሜ 12፥19)። ስለ ሆነም፥ ለኅብረተሰቡ በጎነት ቢመስልም ባይመስልም ጠቅላላው የጥንቆላ መሠረት ኃጢአትና መታለል ነው።

## ለምዋርተኝነት የክርስቲያን ምላሽ ምንድን ነው?

ጌታ ሕዝቡ ለአሁንም ሆነ ለወደፊት በእርሱ እንዲታመን ይፈልጋል። መዝሙር (62)፥8፥ «ዘወትር በእግዚአብሔር ታመኑ» ይለናል (ከ1980 ዓ. ም. አዲስ ትርጉም)። በሌላውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ «በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፥ በራስህም ማስተዋል አትደገፍ፤ በመንገድህ ሁሉ እርሱን እወቅ፥ እርሱም ጎዳናህን ያቀናልሃል» ተብለናል (ምሳሌ 3፥5-6)። መንገዳችንን በጸሎት ለእርሱ አሳልፈን ብንሰጥ፥ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን መረዳት ይሰጠናል። እግዚአብሔር ከእርሱ እንጂ ከምዋርተኞች ምክርንና ምሪትን እንድንሻ አይፈልግም [ዘሌ. 19፥26፤ መዝ. (25)፥12፤ (32)፥8]።

በሕይወታችን የመንገዳችን ብርሃን የሚሆነው የጠንቋዩ (የምዋርተኛ) ምክር ሳይሆን፥ የእግዚአብሔር ቃል ነው [መዝ. (119)፥105]። ስለማናውቀው ነገር በእርሱ መታመን አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ፥ «ምሥጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ (በመጽሐፍ ቅዱስ) የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው» ይላል (ዘዳ. 29፥29)።

## ማጠቃለያ

ምንም እንኳ በዛሬዪቱ አፍሪካ የሕይወት ለውጥ እየታየ ቢሆንም፥ የባህላዊ እምነቶችና ልምምዶች ችግር አሁንም በጣም አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ብዙዎቹ ባህላዊ ሃይማኖቶች እንደ ጠንቋዮችና የአያት ቅድማያት መናፍስት ያሉ አማላጆች፥ የሕይወትን ችግሮች ለማቃለል ወደ እግዚአብሔር እንደሚያቀርቧቸው ያምናሉ። ከዚህም የተነሣ፥ በሥርዓቶች፥ በመሥዋዕቶች፥ በምዋርት፥ በምትሐት፥ በእርግማን፥ በጠንቋይና በአስማት ላይ የሚደረጉ እምነቶች የብዙዎችን አመለካከት ይቀርጻሉ። በተጨማሪም፥ እነዚህ እምነቶች በተለይም ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ደካማ ግንዛቤ ያላቸውን ብዙ ክርስቲያኖች ያሳስታሉ።

በችግር ጊዜ፥ አያሌ ደካማ ክርስቲያኖች ችግሮቻቸውን ለማቃለል አሁንም ወደነዚህ ልምምዶች ይመለሳሉ። በዚህም፥ ሌሎችን አማልክት በእግዚአብሔር ፊት በማስቀመጥ ክርስቲያኖች ከአሠርቱ ትእዛዛት የመጀመሪያውን ይተላለፋሉ (ዘዳ. 5፡7)። እንዲሁም፥ በእነዚህ ኃጢአቶች ላይ በሚወርደው ፍርድ በራሳቸው ላይ መከራን ይጋብዛሉ። ሌሎች አማልክት ያድኑአቸው ዘንድ ስለ ተማመኑባቸው፥ (የሚፈልጉትን) የእግዚአብሔርን ከከፋ ነገር የመጠበቅ ኃይል ያጣሉ። ሰይጣንም የሚፈልገው ይህንኑ ነው! ሰዎች በችግራቸው ጊዜ ምትሐትና ምዋርት የመሳሰሉትን ባሕላዊ ልምምዶች እንዲያደርጉ ይፈትናቸዋል።

ሰይጣን የውሸት አባት ስለ ሆነ፥ ሰዎችን ማታለልና ክርስቲያናዊ ያልሆነ ሃይማኖት ሐሰተኛ አሳቦች በማስፋፋት ከክርስቶስ ማራቅ የሰይጣን ዕቅድ ነው። ስለ ሆነም፥ መጽሐፍ ቅዱስ ሰዎችን በክርስቶስ ከመታመን የሚያርቁትን ከሙታን ጋር መነጋገር፥ ምትሐት፥ ምዋርት፥ ክታብ፥ ድግምት፥ ክርስቲያናዊ ያልሆኑ ሥርዓቶችና መሥዋዕቶች ይኮንናል።

ለክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ አንዱን የእውነት ትክክለኛ አመለካከት እንደሚያስቀምጥ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው። የአያት ቅድማያት መናፍስት፥ በመንፈስ መጠመድ፥ የአካለ መጠን መድረሻ ሥርዓቶች፥ ምዋርት፥ ምትሐት፥ እርግማን፥ አስማት፥ ጠንቋዮችና ሌሎችንም ከባህላዊ እምነቶች ጋር የተያያዙትን ጉዳዮች ከመዳኘታችን በፊት፥ የመጽሐፍ ቅዱስን አመለካከት ልንረዳና ልናምን ይገባል። በተለይም መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሙታንና አንድ ሰው ከሞተ በኋላ ስለሚሆነው ነገር የሚሰጠውን ትምህርት መረዳት አስፈላጊ ነው።

ኢየሱስ ክርስቶስ የነገሥታት ንጉሥና በግዑታይ ዓለም ውስጥ የሚገኙትን መናፍስት ጨምሮ የፍጥረታት ሁሉ አምላክ ነው። በእምነት የቀረበውን ጸሎት በመመለስ፥ እግዚአብሔር ክፉ መናፍስት ወይም ክፉ ሰዎች የሚያመጡትን ማንኛውንም ዓይነት ችግር ለማስወገድ ከሚፈለገው በላይ ብቁ ነው። ክርስቲያኑን ከችግሩ ላለማውጣት ወይም በቀጥታ ችግሩን ላለማቃለል ቢመርጥ እንኳ፥ መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን ለሚወዱት ነገር ሁሉ ለበጎ እንደሚደረግ ያስተምራል (ሮሜ 8፡28)።

ዛሬ በአፍሪካ ክርስቲያኖች ክርስቲያናዊ ካልሆኑ እምነቶች ሁሉ ንስሐ መግባታቸውና ከእነዚህ እምነቶች ጋር የተያያዙትን ዕቃዎች ሁሉ ማውደማቸው በእጅጉ አስፈላጊ ነው። ችግሮች በሚከሰቱበት ጊዜ ክርስቲያኖች ለምሪት፥ ለጥንካሬ፥ ለእርዳታና ከክፉ ለመዳን በጌታ ላይ እንዴት መደገፍ እንዳለባቸው ያውቁ ዘንድ፥ አብያተ ክርስቲያናት አዳዲስ አማኞችን በጌታ ቃል በክርስቶስ ወደሚገኝ ብስለት ማሳደጋቸው በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

በምዕራፍ 13 ላይ የተመሠረቱ የመወያያ ጥያቄዎችና መልመጃዎች

1. መዝሙር (40)፡4 እግዚአብሔር የምትሐትን፥ ከታብንና ድግምትን አጠቃቀም የሚኮንንበትን ምክንያት እንዴት እንደሚያብራራ አሳይ።

2. በምትሐት፥ በድግምት፥ ወዘተ. ከመጠቀም ይልቅ የሕይወትን ችግሮች ለማስወገድ የእግዚአብሔር መንገድ ምንድን ነው? መልስህን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አስደግፍ።

3. በባህላዊ የአፍሪካ ኅብረተሰብ ውስጥ የቀብር ሥርዓቶች አስፈላጊ ክስተቶች የሚሆኑት ለምንድን ነው? ክርስቲያን በቀብር ሥርዓቶች ላይ ምን ዓይነት አመለካከት ሊኖረው ይገባል? አመለካከትህን በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አስደግፍ።

4. የአያት ቅድማያት መናፍስት ምልጃ ሥርዓቶች በዓለም ሁሉ በሚገኙ ባህላዊ ሃይማኖቶች ለምን እንደሚዘወተሩ ተወያዩ። ለእነዚህ ሥርዓቶች የእግዚአብሔር አመለካከት ምንድን ነው?

5. በአያት ቅድማያት ልምምዶችና በጎሰኝነት መካከል የሚገኘውን ግንኙነት አራት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ተከፋፍላችሁ ተወያዩ።

6. ለሞቱት ዘመዶች የክርስትያን አመለካከት ምን መሆን እንደሚገባ አንድ ሰው ለቡድኑ ያብራራ። ተናጋሪው አመለካከቱን ከጉዳዩ ጋር በሚዛመዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ማስደገፍ አለበት።

7. ብዙ ሰዎች፥ የሞቱት ሰዎች ንስሐ ገብተው በክርስቶስ የሚያምኑበት ዕድል ይኖራቸው ይሆን? በማለት ይጠይቃሉ። ለዚህ ጥያቄ ከመጽሐፍ ቅዱስ መልስ ለማግኘት አራት አባላት በሚገኙባቸው ቡድኖች ተከፋፍላችሁ ተወያዩ። የምታገኙአቸውን ጥቅሶች ከየቡድኑ ውስጥ አንድ አንድ ሰው ይጻፍ።

8. መጽሐፍ ቅዱስ በራእይ 21 እና 22 በሚያስተምረው መሠረት መንግሥተ ሰማይን ግለጹ።

9. በመጽሐፍ ቅዱስ ገለጻ መሠረት፥ ከሞት በኋላ ክርስቲያኖችና የማያምኑ ሰዎች ምን ይሆናሉ?

10. ቡድኑ ሕዝቦቻቸው ስለሚጠቀሙባቸው የምትሐትና የመንፈስ መድኃኒት ዓይነቶች ይወያይ። እግዚአብሔር የምትሐትን አጠቃቀም ለምን እንደሚኮንን ግለጹ።

11. የቡድኑ አባላት በአካባቢያቸው በሚከናወኑ ዋንኛ የጥንቆላ ዘዴዎች ላይ ይወያዩ። ሁለት ሰዎች ለተቀሩት የክፍሉ አባላት ምዋርተኝነት ለምን ትክክል እንዳልሆነ ያብራሩ። የምዋርተኝነትን ተግባርና ሐሰተኛ ትንቢትን የሚኮንኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አግኙ።

## SUGGESTED FOR FURTHER READING

Gehman, Richard J. African Traditional Religion in Biblical Perspective. Kijabe, Kenya: Kesho Publications, 1989.

Mbiti, John S. African Religions And Philosophy. London: SPCK, 1969.

Parrinder, Edward G. African Traditional Religion. London: Sheldon Press, 1974.